# አዲስ ዘመን

ኢፕድ


ማክሰኞ | 84ኛ ዓመት ቁጥር 049 ጥቅምት 19 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# ሌላኛው የሀገር አቅም- ዲጂታል ኢኮኖሚ




**ፋንታነሽ ክንዴ**

ኢትዮጵያ ዲጂታል ኢኮኖሚን ለመገንባት እየሠራች ነው። ለዚህም ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂን ቀርጻ እየተገበረች ትገኛለች። በርካታ የመንግሥት አገልግሎቶች በኦንላይን እየተሰጡ ሲሆን፤ የኦንላይን የገንዘብ ዝውውሩም እያደገ መጥቷል። የዜጎችን የዲጂታል እውቀት ለማሳደግም ደግሞ አምስት ሚሊዮን ዜጎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የአምስት ሚሊዮን ኮደሮች ስልጠና በኦንላይን እየተሰጠ ይገኛል።

ለመሆኑ በኢትዮጵያ ዲጂታል ኢኮኖሚን ለመገንባት እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችና የተገኙ ውጤቶች ምን ይመስላሉ? በቀጣይነትስ ከዘርፉ ምን ይጠበቃል?

የዓለም አቀፉ የሞባይል ኮሙኒኬሽን ሲስተም ማህበር (ጂ.ኤስ.ኤም.ኤ) በቅርቡ ይፋ ባደረገው ጥናት፤ በኢትዮጵያ የዲጂታል ኢኮኖሚው ሀገራዊ አስተዋጽኦ በከፍተኛ ደረጃ እያደገ መጥቷል። የሞባይል ኢንተርኔት ግንኙነቶች በ65 በመቶ ያደገ ሲሆን፣ የ4ጂ ሽፋን በስምንት እጥፍ ጨምሯል። በዚህም እ.ኤ.አ. በ2023 ዘርፉ 700 ቢሊዮን ብር ለጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት አበርክቷል። 57 ቢሊዮን ብር የታክስ ገቢም አስገኝቷል።

የሞባይል ኢንተርኔት ተጠቃሚነት እና በቴሌኮም ገበያ ላይ ያለው ውድድር እንዲጨምር ኢትዮ ቴሌኮም እና ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ ትልቅ ሚና እንደነበራቸው የጠቀሰው ሪፖርቱ፤ ዘርፉ እኤአ በ2028 ለአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት አንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር ያበረክታል። ከአንድ ሚሊዮን በላይ አዳዲስ ሥራዎች እንደሚፈጠሩ እና ለመንግሥት 57 ቢሊዮን ብር ተጨማሪ የታክስ ገቢ ያስገኛል ተብሎ እንደሚጠበቅም ይፋ አድርጓል።

በእአአ 2028 ከ50 ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያውያን ከሞባይል ኢንተርኔት ጋር ይገናኛሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ የጠቀሰው ሪፖርቱ፤ ይህም በእአአ 2028 በግብርና ዘርፉ ላይ 140 ቢሊዮን ብር፣ በማኑፋክቸሪንግ ላይ የ114 ቢሊዮን ብር አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

ሌላኛው የሀገር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



በድሉ ውብሸት

## በከተማዋ ዘጠኝ ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር ካፒታል ላስመዘገቡ ባለሀብቶች ፈቃድ ተሰጥቷል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በ2017 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ዘጠኝ ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር ካፒታል ላስመዘገቡ 50 ኢንቨስተሮች ፈቃድ መስጠቱን የደብረ ብርሃን ከተማ አስተዳደር አስታወቀ፡፡ ወደውጭ ከተላኩ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶች ከ185 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ መገኘቱም ተመላክቷል፡፡

የደብረ ብርሃን ተቀዳሚ ምክትል ከንቲባ በድሉ ውብሸት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከተማዋን የኢንቨስትመንት ተመራጭ ከተማ በማድረግ ማህበረሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን በርካታ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛል፡፡

በ2017 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ስድስት ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ብር ካፒታል ላስመዘገቡ 60

በከተማዋ ዘጠኝ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በክልሉ ከመኸር እርሻ ከ50 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ለማግኘት ታቅዷል

- በበጋ መስኖ ከ145 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት ለማልማት እየተሠራ ነው

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ከመኸር እርሻ ከ50 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ለማግኘት መታቀዱን የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ። በበጋ መስኖ ከ145 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት ለማልማት እየተሠራ መሆኑም ተገልጿል።

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ኡስማን ሱሩር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ክልሉ ባለፉት ሶስት ወራት ግብርናን ለማዘመን ፣ ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር በዘርፉ ያሉ ማነቆዎችን ለመፍታት እንዲሁም በመኸር እርሻ ወቅት የተያዙ እቅዶችን ለማሳካት የተቀናጀ የግብርና ልማት ስራዎች በስፋት ተሠርተዋል።

በመኸር እርሻ ወቅት ክልሉ 564 ሺህ ሄክታር በማልማት ከ50 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ለማግኘት አቅዶ እስካሁን 550 ሺህ ሄክታር መሬት ለምቷል ብለዋል።

በዝናብ ስርጭት መብዛት ምክንያት በአንዳንድ አካባቢዎች የስንዴ ዘር ያለተዘራ መሆኑን ያነሱት የቢሮ ኃላፊው፤ ያንን ለማካካስም ከነሐሴ መጨረሻ ጀምሮ ባለው የጸደይ ወቅት ተጨማሪ 16 ሺህ ሄክታር መሬት ስንዴ መልማቱን ጠቁመዋል።

በመኸር እርሻው የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ፣ የአርሶ አደሩ የማሳ አያያዝ፣ የተባይና አረም መከላከል ሥራው በጥሩ ሁኔታ መሆኑንና የማሳ ሰብሎች ቁመናም ምርታማነት የሚጨምር መሆኑን ያሳያሉ ሲሉ ገልጸዋል።

በክልሉ ከመኸር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




አቶ ኡስማን ሱሩር




# ምክክር የዘላቂ ሰላም ምንጭ

ጌትነት ምህረቴ

ዜና ሀተታ


ቀሲስ በድሉ ፈቀደ


ወይዘሮ ገነት አደኝ


ዮናስ አዳዬ (ዶ/ር)

የሃይማኖት አባት ናቸው። ሰዎች ሲጣሉ መክረውና ገስጸው አስታርቀዋል። ስለ ሀገር ሰላምም መስበክ የስብከት ስራቸው አካል ነው። ቀሲስ በድሉ ፈቀደ። እኚህን አባት ያገኘናቸው ወላይታ ሶዶ ከተማ ነው። በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል እየተካሄደ ያለውን የሀገራዊ ምክክር የአጀንዳ ማሰባሰብና የተወካዮች ልየታ ለመሳተፍ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ከጋሞ ዞን ገረሱ ወረዳ እንደመጡ ይናገራሉ። እንኳን ለሀገር ሰላም ይቅርና በግለሰብ ደረጃ ለመግባትም፣ ሃሳብ ለመስጠትና ህይወትን ለመለወጥም መመካከር ብዙ ጥቅም አለው ይላሉ።

አሁን የመጣንበት ዓላማ ትልቅ ነው። ከግለሰብ አልፎ የሀገርን ሰላምና አንድነት የሚያጸና ነው። በህዝቦች መካከል የጋራ መግባባት የሚጎለብትና የሚያጠብቅ ነው። ሀገራዊ ምክክሩ ለኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም የሚያመጣ በመሆኑ በእጃችን የያዝነው ወሳኝ ዕድል መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ ይህን ዕድል በአግባቡ መጠቀም የሁሉም ኢትዮጵያዊ ድርሻ መሆኑን ያመለክታሉ።

“ወጥቶ ለመግባት፣ተምሮ ለመለወጥ፣ ነግዶ ለማትረፍ፣የሰላም መረጋገጥ ያስፈልገናል። ሃይማኖትም ቢሆን ያለሰላም ዋጋ የለውም’’ የሚሉት ቄስ በድሉ፤የታጠቁ ወገኖቻችን ከአውዳሚ ተግባር ተመልሰው ለውይይትና ለምክክር ዕድል መስጠት ይጠበቅባቸዋል ።ምክንያቱም ጦርነትም ሆነ ግጭት መቋጫው ምክክር ነው ብለዋል። ከዚህ መነሻነት የከፉ ጉዳትና ውድመት ከመድረሱ በፊት ልዩነቶችንና ችግሮችን በምክክር መፍታት ከአሁን ጀምሮ መለማመድና ባህል ማድረግ ይኖርብናል ሲሉ መክረዋል።

ለእኔ ኢትዮጵያ ሀገሬም እናቴም ናት። በዕድገት እየገሰገሰች እንድትሄድ እፈልጋለሁ። ህዝቡ ከድህነት እንዲወጣ ፍላጎቴ ነው። ለዚህ ደግሞ ሰላም ያስፈልጋል። ምክክሩ የኢትዮጵያ ችግሮችን ቋጠሮ ይፈታል ብዬ ስለማምን እኔም የድርሻዬን እየተወጣው ነው ሲሉ ገልጸውልናል ።

ሴት አርሶ አደሮችን ወክለው ተመርጠው ከደራማሎ ወረዳ እንደመጡ የሚናገሩት ወይዘሮ ገነት አደኘ፣ የግብርና ስራዬን ጥዬ የመጣሁት ምክክሩ ለሀገራችን ዘላቂ ሰላም ያመጣል ብዬ ስለማምንና ከፍተኛ ፍላጎት ስላለኝ ነው ያሉት። ሰላም ከሌለ አርሶ አደሩ ምርት ለማምረት ይቸገራል፣ምርቱን በሚፈልገው ዋጋ መሸጥ አይችልም። ሀገራዊ ምክክሩ በሀገራችን ልዩነቶች በምክክር ተፈትተው ሰላም ስለሚያረጋግጥ እየተሳተፍኩ እገኛለሁ ብለዋል።

የኢትዮጵያ ሰላም መሆን ለእኛ ሰርቶ መለወጥ ቀላል ነው ያሉት አርሶ አደሯ፣ በተለይ እናቶች ሰላም ብዙ ነገራቸው ነው። ይህ ሀገራዊ ምክክር እንዲሳካም በጸሎትም በተሳትፎም በግንባር ቀደምትነት መሳተፍ አለብን ነው ያሉት።

ኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር ዮናስ አዳዬ (ዶ/ር) በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ ሶዶ ከተማ የአጀንዳ የማሰባሰብ የምክክር መድረኩን መጀመር አስመልክቶ እንዳሉት፤ኢትዮጵያ እኛን በውብ ባህልና እሴቶች ያላበሰች ሀገር ናት። የሀሳብ ልዩነቶች ሀገራችንን እየፈተኗት ነው። እነዚህን ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት ሀገራዊ ምክክር እየተካሄደ ነው።

እስካሁን ሰባት ክልሎችና በሁለት ከተማ አስተዳደሮች በክልል ደረጃ የአጀንዳ ማሰባሰብና የተወካዮች መረጣ በስኬት መካሄዱን አውስተው፣ በቀሪ ክልሎችም ለማካሄድ አስፈላጊው ዝግጅት መደረጉን ይጠቁማሉ ።

በደቡብ ኢትዮጵያ በክልል ደረጃ የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍ ለስድስት ተከታታይ ቀናት እንደሚካሄድ ይናገራሉ። በክልል ደረጃ በሚካሄደው የአጀንዳ ማሰባሰብ ምዕራፍ በጥልቀት በመመካከር አጀንዳዎችን የማሰባሰብና በሀገራዊ ምክክር የሚሳተፉ ተወካዮች መረጣ እንደሚካሄድም ይጠቁማሉ፡፡

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ከጥቅምት 18 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ለስድስት ቀናት እየተካሄደ የሚገኘው የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍም የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የሲቪል ማህበረሰ፣ተጽእኖ ፈጣሪ ሰዎችና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ተወካዮች በመሳተፍ ላይ መሆናቸውን ይገልፃሉ። በምክክሩም ከ12 ዞኖች ውስጥ በሚገኙ 96 ወረዳዎች የተወጣጡ የህብረተሰብ ክፍሎች እየተሳተፉ ይገኛሉ።

ይህ ታሪካዊ ሀገር የማሻገር ተልዕኮ እንዲሳካ ህብረተሰቡና የሚመለከታቸው አካላት የበኩላቸውን ላቅ ያለ ድርሻ እንዲወጡ ጥሪ ያቀርባሉ ።

# በክልሉ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ኩንታል ምርት ተሰብስቧል

ታደሠ ብናልፈው

አዲስ አበባ፡- በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በ2016/17 ዓ.ም የምርት ዘመን በመኸር ወቅት የተዘሩና ቀድመው የደረሱ ሰብሎችን በመሰብሰብ ስራ እስካሁን ከአንድ ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት መሰብሰብ መቻሉን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ።

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ግብርና ቢሮ ምክትልና የእርሻ ዘርፍ ኃላፊ አቶ አድማሱ አወቀ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2016/17 ዓ.ም የምርት ዘመን በመኸር ወቅት የተዘሩና ቀድመው የደረሱ ሰብሎች በሰው ኃይል የመሰብሰብ ስራ እየተከናወነ ነው። በዚህም ከ13 ሺህ ሄክታር ማሳን በመሰብሰብ ከአንድ ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ተገኝቷል።

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ቀድመው የደረሱ የመኸር ሰብሎች ጊዜያቸውና ወቅታቸው ተላልፎ የምርት ብክነት እንዳይከሰት በሰው ኃይል የመሰብሰብ ስራ እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል።

በክልሉ ቀድመው የደረሱ ሰብሎችን ለመሰብሰብ አመራሮችና ባለሙያዎች ወደየወረዳዎችና ቀበሌዎች በመሰማራት ማህብረሰቡን የማነሳሳትና የመቀስቀስ ስራ እየሰሩ እንደሚገኙ ገልፀዋል። ቀደመው የደረሱ ሰብሎችን በጊዜያቸውና በወቅታቸው በመሰብሰብ የክልሉን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ እየተሰራ ያለው ስራ ተጠናክሮ መቀጠሉንም አብራርተዋል።

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በ2016/17 ዓ.ም የመኸር ወቅት የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተለያዩ አዝርእቶችንና ቋሚ ሰብሎችን ጨምሮ የማልማት ስራ ተሰርቷል ያሉት ምክትል ኃላፊው፤ ከዘሩትም ሰብሎች ውስጥ ጤፍ፣ ቦሎቄ፣ማሾና የሆርቲካልቸር ሰብሎች ደርሰው እየተሰበሰቡ መሆኑን ገልጸዋል።

በክልሉ የደረሱ ሰብሎች በዝናብ እንዳይበላሹ በወቅታቸው የመሰብሰብና የመውቃት ስራ እየተሰራ ነው፤ እስካሁን ማለትም ጥቅምት 15/ 2017 ዓ.ም ድረስ ከ13 ሺህ ሄክታር በላይ ማሳ የመሰብሰብ ስራ ተከናውኖ ከአንድ ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት መገኘቱን ተናግረዋል።

አርሶ አደሮች የደረሱ ሰብሎች ሲሰበስቡና ሲወቁ በጥንቃቄ በመሰብሰብና በመውቃት የምርት ብክነትን ሊከላከሉ ይገባል ብለዋል።

እንደ አቶ አድማሱ አባባል፤ በክልሉ የስንዴ ሰብልን ምርታማነት ለማሳደግና የምርት ብክነትን ለመከላከል በኮምባይነር የመሰብሰብ ስራ እየተሰራ ነው። በ2016/17 ዓ.ም የምርት ዘመን በመኸር ወቅት ሰባት መቶ 15 ሺህ 945 ሄክታር የእርሻ መሬትን በተለያዩና በቋሚ ሸብሎች የመሸፈን ስራ ተከናውኗል። በተለያዩና በቋሚ ሰብሎች በዘር ከተሸፈነው ሰባት መቶ 15 ሺህ 945 ሄክታር መሬትም 60 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይሰበሰባል ተብሎ ይጠበቃል።

የክልሉ አርሶ አደሮች ቀድመው የደረሱ ሰብሎች በጊዜያቸውና በወቅታቸው እንዲሰበሰቡና ወቅተው ወደ ጎተራ እንዲያስገቡ ጥሪ አቅርበዋል።

# በመዲናዋ በበጀት ዓመቱ 300 ሺህ ቶን የአማቂ ጋዝ ልቀት ለመቀነስ ታቅዷል

ልጅዓለም ፍቅሬ



አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ በተያዘው በጀት ዓመት 300 ሺህ ሜትሪክ ቶን የአማቂ ጋዝ ልቀት ለመቀነስ ታቅዶ እየተሰራ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አስታወቀ።

በአዲስ አበባ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአማቂ ጋዝ ልኬት፣ ቅነሳና አረንጓዴ ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ቡድን መሪ አቶ ሰለሞን መለሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤በመዲናዋ በበጀት ዓመቱ 300 ሺህ ቶን የአማቂ ጋዝ ልቀት ለመቀነስ ታቅዷል።

በባለፈው በጀት ዓመት 250 ሺህ ቶን ያህል ለመቀነስ ታቅዶ 255 ሺህ ቶን መቀነስ ተችሏል ያሉ ሲሆን፤ በተያዘው በጀት ዓመትም 300 ሺህ ቶን የአማቂ ጋዝ ልቀት ለመቀነስ ታቅዶ እየተሰራ ይገኛል።

እንደ አቶ ሰለሞን ገለጻ፤ በ2012 በተደረገ የአማቂ ጋዝ ልኬት ሰባት ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የነበረው በ2014/15 ዓ.ም ሰባት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ሆኗል፡ ፡ በየዓመቱ አማቂ ጋዞች ከሚመነጭባቸው ዘርፎች መካከል ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት አሁንም ከአሮጌ መኪናዎች የሚወጣው ነው።

አቶ ሰለሞን አክለውም፤ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ያለው ልዩነት ከአምስት መቶ ሺህ በላይ መሆኑ በከተማው የአማቂ ጋዝ ሁኔታ እየጨመረ መምጣቱንና ለጤና አስጊ ደረጃ የሚያደርስ መሆኑን አመላካች ነው ብለዋል።

ከመስፈርት በላይ የአየር ብክለት የሚያስከትሉ አሮጌ መኪናዎች ለመቆጣጠር የወጣው መመሪያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተግባራዊ መሆን ይጀምራል ያሉት አቶ ሰለሞን፤ የኮንስትራክሽን ብናኝ በአግባቡ ማስወገድ የሚቻልበት መመሪያም እየተዘጋጀ መሆኑን ጠቁመዋል።

በተጨማሪም ወደ ረጂ የሚወሰደው ደረቅ ቆሻሻ በመቀነስ በኮምፖስ መልሶ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ በዘርፉ የተሰማሩ የተለያዩ ማህበራት እንዲጠናከሩ እየተደረገ መሆኑንም ጠቁመዋል።

አቶ ሰለሞን፤ ባለስልጣኑ ችግሩን ከመቀነስ ጎን ለጎን የኤሌክትሪክ መኪኖች እንዲበራከቱ እንዲሁም ተጠቃሚው በብዛት የከተማ አውቶቡሶች እንዲጠቀሙም ለማድረግ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር እየተሰራ መሆኑን አመልክተዋል። በሀገሪቱም የተለያዩ የጤና ችግሮች ከመድረሳቸው በፊት የግንዛቤ ስራ የመስራትና ህጋዊ እርምጃ መውሰድ በሚያስፈልግበት ላይ እርምጃ እየተወሰደ መሆኑን አብራርተዋል።

እስከ እአአ 2050 ድረስ ከምንም አይነት አየር ብክለት የጸዳች ከተማ ለመፍጠር ውጥን ተይዟል ያሉት አቶ ሰለሞን፤ አሁን ላይ ባለው ሂደትም የኤሌክትሪክ መኪናዎች መግባት፣የመንገዶች መስፋት እና የከተማ አውቶቡሶች መበራከት ከጀመሩ ወዲህም የተወሰነ ለውጥ እንዳለ የሚጠቁሙ ነገሮች እንዳሉ አስረድተዋል።

በከተማው ያለው የአማቂ ጋዝ መጠን ምን ደረጃ እንደደረሰ በየሁለት ዓመቱ የመለካት ስራ እንደሚሰራና የ2015/16 ዓ.ም በተያዘው በጀት ዓመት ጥናት እንደሚደረግ አንስተዋል።



አቶ ሚኒሊክ ጌታሁን

# ከሀገር ውስጥ የኤሌክትሪክ ሽያጭ ከአምስት ቢሊዮን ብር በላይ ተገኘ

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ሶስት ወራት ከሀገር ውስጥ የኤሌክትሪክ ሽያጭ ከአምስት ቢሊዮን ብር በላይ መገኘቱን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሀይል አስታወቀ፡፡

በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሀይል የሽያጭና ገቢዎች አስተዳደር ስራ አስኪያጅ ሚኒሊክ ጌታሁን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ተቋሙ የሚያመርተውን ሀይል ለሀገር ውስጥ ደንበኞች እንዲሁም ለተለያዩ ጎረቤት ሀገራት በሽያጭ ያቀርባል፡፡

በሀገር ውስጥ ሽያጭ ከሚያቀርብላቸው ደንበኞቹ መካከል ዋነኛው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሲሆን ባለፉት ሶስት ወራት 9 ሺ 128 ነጥብ 08 ሜጋ ዋት ሀይል በማስተላለፍ ከሶስት ቢሊዮን 297 ሚሊዮን ብር በላይ ማግኘቱን ገልጸዋል፡፡

ተቋሙ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በተጨማሪ ለከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች እንዲሁም ለኢትዮ ጅቡቲ ምድር ባቡር ሀይል የሚያቀርብ ሲሆን፤ ከእነዚህ ተቋማት ሁለት ቢሊዮን ሚጠጋ ብር ማግኘቱን ተናግረዋል፡፡

በጥቅሉ ተቋሙ ከሀገር ውስጥ የኤሌክትሪክ ሽያጭ አምስት ቢሊዮን 412 ሚሊዮን ብር ለመሰብሰብ አቅዶ አምስት ቢሊዮን 226 ሚሊዮን ብር በላይ በመሰብሰብ የእቅዱን 96 በመቶ ማሳካት መቻሉን ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሀይል ከብሄራዊ ባንክ በሀገር ውስጥ ዶላር የማንቀሳቀስ ፍቃድ ያለው ተቋም መሆኑን የገለጹት አቶ ሚኒሊክ፤ አንዳንድ ተቋማትን በዶላር እንደሚያስከፍል ተናግረዋል፡፡ በዚህም በሶስት ወሩ በሀገር ውስጥ በዳታ ማይኒንግ ላይ ለተሰማሩ ተቋማት ከ27 ሚሊዮን ዶላር በላይ ሽያጭ ማከናወኑን ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ በአሁኑ ሰአት ለጅቡቲ ፣ለሱዳን እንዲሁም ለኬንያ የኤሌክትሪክ ሀይል ሽያጭ የምታቀርብ ሲሆን በዘንድሮው ሩብ አመትም ለጅቡቲ 169 ሺ 710 ነጥብ 91 ሜጋ ዋት ሀይል በማስተላለፍ 10 ሚሊዮን 379 ዶላር ፣ለሱዳን 13ሺ 185 ነጥብ 50 ሜጋ ዋት ሀይል በማስተላለፍ 659 ሺ 275 ዶላር ፣ለኬንያ 314 ሺ 931 ነጥብ 38 ሜጋ ዋት ሀይል በማስተላለፍ ከ20 ሚሊዮን 470 ሺ ዶላር የተገኘ ሲሆን፤ በጥቅሉ ተቋሙ ለጎረቤት ሀገራት በሸጠው ሀይል ከ31 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ማግኘቱን አብራርተዋል፡፡

አቶ ሚኒሊክ ለሱዳን የቀረበው ሀይል ለማቅረብ ከታቀደው 15 በመቶው ብቻ መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህም ሱዳን ካለባት የጸጥታ ችግር አንጻር በአግባቡ ክፍያ ባለመፈፀሟ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

# የማህበረሰብ ፍትህን ለማቋቋም የሚያስችል ስምምነት ተፈረመ

**ዘላለም ግዛው**




አዲስ አበባ፡- ፍትህ ሚኒስቴር ሄግ ከተባለ የሕግ ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር በመሬት ጉዳይ የሚነሱ አለመግባባቶች እና ግጭቶችን ወጪ ቆጣቢ እና ማህበረሰብን ማዕከል ባደረገ መልኩ መፍትሄ እንዲያገኝ የሚያስችል ስምምነት ተፈራረመ።

መርሀ ግብሩን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችለውን ስምምነት የፍትህ ሚኒስትር ዴኤታ ኤርሚያስ የማነብርሃን (ዶ/ር) እና የሄግ ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት መስራችና ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሳሙኤል ሙለር (ዶ/ር) ትናንት ተፈራርመዋል።

ስምምነቱ በሶስት ማዕከላት የማህበረሰብ ፍትህን ለማቋቋም ያስችላል ያሉት ኤርሚያስ(ዶ/ር)፤ ለማእከላቱ ለሚያስፈልጉ ወጪዎች እና ግብአቶች እንዲሁም በማእከሉ ለሚሰሩት አሸማጋዮች ክፍያ ድጋፍ የሚደረግበት መሆኑን ገልጸዋል።

ትግበራው በኢትዮጵያ የፍትህ ሥርዓት ውስጥ አዲስ ምዕራፍ የከፈተና አዎንታዊ ሚና የሚኖረው መሆኑን የጠቆሙት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ማዕከላቱን በማቋቋምና በማጠናከር የመሬት ጉዳይ ከመደበኛ ሥርዓት ውጪ በኢ-መደበኛ ሥርዓት በባህላዊ መንገድ በአሸማጋዮች እንዲፈታ የሚያስችል ነው ብለዋል።

ትግበራው የማህበረሰብ ፍትህን ለማስፋፋት የሚያስችል መሆኑን የገለጹት ኤርሚያስ የማነብርሃን(ዶ/ር)፤ በአዲስ አበባ ከተማ፣ በሲዳማ እና በአፋር ክልሎች በሙከራ የሚተገበር መሆኑን ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ አለመስማማት ይነሳባቸዋል ተብለው ከሚጠቀሱት የቤተሰብ ጉዳይ እና የውርስ ግጭት በበለጠ ዋነኛው የመሬት ጉዳይ ነው። የመሬት ጉዳይ ከኢኮኖሚ ጉዳይ ባለፈ የማንነትና የማህበራዊ ይዘት ያለው እና ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ነው ሲሉም አክለዋል።

እንደርሳቸው ገለጻ፤ በሂል አማካኝነት የተደረገ ጥናት እንደሚያሳየው፤ በዓመት ወደ ሁለት ሚሊዮን የሚጠጉ መሬት ላይ መሰረት ያደረጉ ግጭቶች ይነሳሉ።

ስምምነቱ በመሬት ጉዳይ የሚነሱ አለመግባባቶች እና ግጭቶችን ማህበረሰብን ማዕከል ባደረገ፣ አሸማጋዮችን ባሰባሰበ እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ለመፍታት የሚተገበር ነው።

በኢትዮጵያ ከሕገ መንግስቱ ጀምሮ የመሬት ውርስ፣ የመሬት ይዞታ፣ የድንበር ማካለል፣ የመሬት ግጦሽ፣ በግለሰቦች መካከል የሚያጋጥሙ አለመግባባቶች እና በማህበረሰቦች መካከል የሚያጋጥሙ ግጭቶች የሚፈቱበት የዳበረ የህግ ስርዓት መኖሩንም አመላክተዋል።

የትራንስፎርሜሽን ትግበራ፣ የአቅም ግንባታ እና የቴክኒክ ድጋፎችን በጋራ ለመስራት እንደሚያስችል በስምምነቱ ወቅት የተገለጸ ሲሆን፤ በቀጣይ የማዕከላቱን ውጤት በመመልከት በሁሉም አካባቢዎች እንዲስፋፋ እንደሚደረግም ተገልጿል።



# ከተማዋ ያላትን ፀጋ በመጠቀም ጥራት ያለው የምግብ ተዋፅኦ ለማምረት እየተሠራ ነው

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- አዲስ አበባ ያላትን ፀጋ በመጠቀም ጥራት ያለው የምግብ ተዋፅኦ በማምረት የኑሮ ውድነቱን ለማቅለል እየተሰራ መሆኑ ተገለጸ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ የአርሶአደር ከተማ ግብርና ልማት ኮምሽን ባለሙያ አቶ ተስፋዬ ኪዳኔማርያም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ በዕፅዋት እና በእንስሳ ዘርፍ ከፍተኛ የልማት ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡ በአትክልት ልማት ዘርፍ ከአምስት መቶ ሺ በላይ ተጠቃሚዎች ራሳቸውን ችለው ገበያውን የማረጋጋት ስራ እየሰሩ ነው፡፡

በተያዘው ዓመትም በሁሉም ክፍለ ከተሞች ጥራት ያለው ምርት ለማምረት በዕቅድ እየተሰራ መሆኑን በመጥቀስ፤ በዋናነት የከተማ ነዋሪ ባለችው መሬት ላይ የራሱን ፍጆታ ከገበያ ከመግዛት ይልቅ በራሱ አምርቶ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ነው ብለዋል፡፡

በከተማዋ ከሰባት ሺ በላይ ሄክታር መሬት በአትክልት በመሸፈን ምርት ለማግኘት እየተሰራ መሆኑን ገልፀው፤ ይህም የገበያ መረጋጋት ላይ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው አመልክተዋል፡፡ ከስራ ዕድል ፈጠራ ጋር በተያያዘ ደግሞ ከአምስት መቶ ሺ በላይ በማህበር እና በግል በግብርናው ዘርፍ እየተሳተፉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በተያዘው ዓመት ነባሩን ስራ በማስቀጠል ምርትን ለማሳደግ መታቀዱን ጠቅሰው፤ጥራት ያለው እና ደህንነቱ የተጠበቀ ምርት ለገበያ እንዲያመርት እየተሰራ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

የከተማ ግብርናው እንዳይጎለብት ከሚያደርጉት ጉዳዮች መካከል ከፍተኛ የባለሙያ እጥረት ዋነኛ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ የህብረተሰቡ ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ቢሆንም ከባለሙያ ጋር ባለመመጣጠኑ ዘርፉ ውጤታማ እንዳይሆን ማድረጉን ጠቅሰዋል፡፡

በተጨማሪም የግብአት አቅርቦት የዘር፣ የተለያዩ እርሻ መሳሪያዎች ዋጋ መጨመር የከተማ ግብርናው አስቸጋሪ እንዲሆን ማድረጉንም አስረድተዋል፡፡ ለምሳሌ አንድ ኪሎ የአትክልት ዘር (ቆስጣ፣ቲማቲም እና ሰላጣ) በፊት ከአምስት መቶ እስከ አንድ ሺ ብር ይሸጥ የነበረ ቢሆንም አሁን እስከ ሶስት ሺ ብር መድረሱ እንቅፋት መፍጠሩን ተናግረዋል፡፡

አሁን ላይ በአዲስ መልክ እየተሰራ ያለው የከተማ ግብርና ቅንጅት የሚያስፈልገው መሆኑን ጠቅሰው፤ ቴክኖሎጂ አለመጠቀም እና በቂ ባለሙያ ባለመኖሩ ለዘርፉ እንቅፋት መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ከተማዋ ያላትን ፀጋ በአግባቡ በመጠቀም በተለይ የሀገር ውስጥ ማዳበሪያ በማምረት ውጤታማ ስራ ለመስራት ዕቅድ መያዙን ጠቅሰዋል፡፡

# ሌላኛው የሀገር አቅም - ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በኢትዮጵያ ያለውን የዲጂታላይዜሽን አቅም ሙሉ በሙሉ ለመጠቀም በተመጣጣኝ ዋጋ አገልግሎት አቅርቦትን ማመቻቸት፣ ፈጣን የቴሌኮም ማሻሻያ ማድረግ፣ የሞባይል ቀፎዎችን ዋጋ ተመጣጣኝነት ማሻሻል፣ የሞባይል ገንዘብ ዝውውር አገልግሎቶችን ማስፋፋት እንዲሁም የዲጂታል ክህሎትን እና የመንግሥት አገልግሎቶችን ማሳደግ የሚሉ ጉዳዮችን ማህበሩ በምክረ-ሃሳብነት አቅርቧል።

የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ፍሬሕይወት ታምሩ እንደሚሉት፤ ኢትዮጵያ ኢኮኖሚውን በጂጂታል ቴክኖሎጂ ለማገዝ እያከናወነች ያለው ሥራ ውጤታማ ሆኗል። ለአጠቃላይ ሀገራዊ ምርትም ስምንት በመቶ አስተዋጽኦ አድርጓል።

ባለፉት ስድስት ዓመታት በተወሰዱ እርምጃዎች ሀገሪቱ ቀደም ሲል ከነበራት የኢንተርኔት ተደራሽነት እያደገ መጥቷል የሚሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ፤ ይህም ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ላይ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ሀገሪቱን በአፍሪካ ደረጃም ተጠቃሽ አድርጓታል።

በእኤአ 2018 የሞባይል ተጠቃሚዎች ቁጥር 37 ሚሊዮን እንደነበር አስታውሰው፤ አሁን ላይ 79 ሚሊዮን መድረሱን ጠቁመዋል። የኢንተርኔት ተጠቃሚዎችም ከ16 ሚሊዮን ወደ 46 ሚሊዮን ማደጉን አንስተው፤ ዛሬ ላይ 424 ከተሞች የ4ጂ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል። የስማርት ስልክ ተጠቃሚዎች ቁጥርም 34 ሚሊዮን ደርሷል።

ገጠሩ አካባቢ ማህበረሰብ የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል በተመጣጣኝ ዋጋ የዘመናዊ ስልክ ቀፎ የማቅረብ ሥራ የተከናወነ ሲሆን በቀጣይነትም ይህ ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ያመለክታሉ።

ሥራውን ማስፋት አስፈላጊ በመሆኑም በተያዘው ዓመት አንድ ነጥብ አንድ ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ተመድቧል የሚሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ፤ ከዚህም ተጨማሪ 400 ከተሞች የ4ጂ፣ 15 ከተሞች ደግሞ የ5ጂ አገለግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረጉን ያስረዳሉ።

በትብብር የሚከናወኑ ሥራዎች ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ እንደሚያስችሉ አመላክተው፤ ለዚህም ሁሉም ባለድርሻዎች ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪ ያቀርባሉ።

በትምህርት ሚኒስቴር የአይሲቲና ዲጂታል ትምህርት መሪ ሥራ አስፈጻሚ ዘላለም አሰፋ(ዶ/ር) በበኩላቸው እንደሚናገሩት፤ ማንበብና መጻፍ የሚችል ትውልድ ለማፍራት እንደሚሠራ ሁሉ የዲጂታል ክህሎት ያለው ዜጋ ለማፍራትም በትኩረት እየተሠራ ነው። ለዚህ አስቻይ የሆኑ የተለያዩ ስትራቴጂዎችና ፖሊሲዎች ተቀርጸው እየተተገበሩ ነው።

የአይሲቲ ትምህርት ከታች ጀምሮ እንዲሰጥ ማድረግ እና በተለይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራንን የዲጂታል ክህሎት እንዲኖራቸው ለማስቻል እየተሠራ መሆኑን ይጠቅሳሉ። ከዚህም ባለፈ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከትምህርት ውጪ ላለው ማህበረሰብ የዲጂታል ክህሎትን የሚያሳድጉ ስልጠናዎችን እየሰጡ ነው። በቀጣይነትም ለሁሉም ዜጋ የዲጂታል ክህሎት ማበልጸጊያነት የሚያገለግል ሥርዓተ ትምህርት እየተዘጋጀ መሆኑንም ይገልጻሉ።

# በክልሉ ከመኸር እርሻ ከ50 ሚሊዮን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በተለይም በጋሞ አካባቢ የተጎዱ መሬቶች ላይ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ በስፋት የተሰራ ሲሆን፤ አሲዳማ መሬቶች ያሉባቸው አካባቢዎች ደግሞ የአፈር ህክምና ተደርጎ በክላስተር እንዲለማ ተደርጓል ብለዋል።

እንደ አቶ ኡስማን ገለጻ፤ የደረሱ ሰብሎች በወቅቱ መሰብሰብ አስፈላጊ በመሆኑ ከጥቅምት ወር ጀምሮ የተለያዩ ንቅናቄዎች እየተደረጉ ነው። እስካሁን 60 ሺህ በላይ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች በንቅናቄው መሳተፋቸውን ተናግረዋል።

ንቅናቄው በመኸርና በበልግ የለሙ ምርቶችን ከብክነት በጸዳ መልኩ መሰብሰብ ፣ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሰብሎችን እንዳያበላሽ፣ እንዲሁም በቴክኖሎጂ የተደገፈ ምርት አሰባሰብ ላያ ያተኮረ ሲሆን፤ በዚህም ተጨባጭ ውጤት እየተመዘገበ መሆኑን አመላክተዋል።

የቢሮ ኃላፊው፤ በተቀናጀ የግብርና ልማት ሥራ በበጋ መስኖ 146 ሺህ ሄክታር መሬት በማረስ 35 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ታቅዶ ወደ ተግባር ተገብቷል ። በበጋ መስኖ ከሚታረሰው መሬት 141 ሺህ ሄክታሩ በአትክልት፣ ፍራፍሬ እና በስራስር የሚሸፈን ሲሆን፤ የተቀረው መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ የሚሸፈን መሆኑን አስረድተዋል።

በአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ ረገድ የተሠሩ ሥራዎችን በተለመለከተ በመኸር ወቅት ክልሉ በአንድ ጀንበር አምስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ችግኝ ለመትከል ታቅዶ ዘጠኝ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ችግኝ መተከሉን ያስታወሱት አቶ ኡስማን፤ ከችግኝ መትከል ባለፈም ወንድማማችነትና አንድነት ያጎለበተ ነበር ሲሉ ገልጸዋል።

# በከተማዋ ዘጠኝ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ፤ ዘጠኝ ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር ካፒታል ላስመዘገቡ 50 ባለሀብቶች ፈቃድ መሰጠቱን አስታውቀዋል፡፡

ፈቃድ ባወጡ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ለስድስት ሺህ 188 ዜጎች የሥራ እድል ሊፈጠር እንደሚችል አመላክተዋል፡፡ በአግሮ ፕሮሰሲንግ 27፣ በጨርቃጨርቅ ሶስት፣ በኬሚካል 20፣ በእንጨትና ብረታ ብረት 16 በአገልግሎት ዘርፍ ሰባት በድምሩ 66 ፕሮጀክቶች መለየታቸውን ተናግረዋል፡፡

በሩብ ዓመቱ ስድስት የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ወደ ግንባታ ለማስገባት ታቅዶ የ12 ፕሮጀክቶች ግንባታን በማስጀምር ከእቅድ በላይ መከናወን መቻሉን ጠቁመዋል፡፡ አምስት አምራች ኢንዱስትሪዎች ወደ ምርት መግባታቸውን እና የአምስት ፕሮጀክቶች ግንባታ መጠናቀቁንም ጨምረው ገልጸዋል፡፡

በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ወደ ውጭ ምርታቸውን ከሚልኩ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች 185 ሚሊዮን 378 ሺህ ዶላር ገቢ መገኘቱን አስታውቀዋል፡፡

ገቢ ምርትን የሚተኩ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶችን በመለየት፣ ተኪ ምርት የሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍና የምረት መጠንን እንዲጨምሩ በማድረግ አምስት ሚሊዮን 711 ሺህ 855 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ማዳን መቻሉን አስረድተዋል፡፡

በሌላ በኩል የመሬት ካሳ ከፍለው ሰባት ባለሀብቶች መሬት ያገኙ ሲሆን፤ ስድስት ነጥብ 27 ሄክታር መሬት መተላለፉን ጠቁመዋል፡፡ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውልና መሰረተ ልማት የተሟላለት 73 ነጥብ 88 ሄክታር መሬት ተዘጋጅቶ 39 ነጥብ 72 ሄክታር ማስተላለፍ መቻሉን አብራርተዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ትግበራ ያስገኘውን ውጤት ማላቅ ይገባል!

በቅርቡ በተካሄደው የ100 ቀናት አፈጻጸም ግምገማ በ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት በተለያዩ ዘርፎች ላቅ ያሉ እድገቶች መመዝገባቸው ተመላክቷል። የተሟላ ማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ትግበራው ደግሞ ለእዚህ የተሻለ አፈጻጸም አስተዋጽኦ ማድረጉም ተገልጿል። ይህ አፈጻጸም በበጀት ዓመቱ እንዲመዘገብ የተቀመጠው እድገት እንደሚሳካ አመላካች መሆኑም ተጠቁሟል።

በተለይ በወጪ ንግድ ፣በመንግሥት ገቢ፣ በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት እና በውጭ ምንዛሬ ግኘት የተሻለ አፈጻጸም ተመዝግቧል። ከወጪ ንግድ አኳያም በማዕድን በተለይ በወርቅ የወጪ ንግድ እጅግ ስኬታማ ተግባር ተከናውኗል። በዚህ ረገድ ማሳያ የሚሆነው ደግሞ፤ በ2016 በጀት ዓመት ዓመቱን ሙሉ ወደ ብሄራዊ ባንክ የገባው የወርቅ መጠን አራት ቶን ብቻ የነበረበት ሁኔታ፤ በተያዘው በጀት አመት የመጀመሪያው ሩብ አመት ወይም ሶስት ወራት ብቻ ሰባት ቶን ወርቅ ወደ ብሄራዊ ባንክ መግባቱ ነው።

ይህም የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ምን ያህል ለውጥ እንዳመጣ ይጠቁማል፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የወርቅ ምርትን በከፍተኛ ደረጃ እያሳደገ መሆኑን የማእድን ሚኒስቴር መረጃም አረጋግጧል። በተለይ ማሻሻያው የማእድን አምራቾችን ተጠቃሚ በማድረጉ አምራቾች የተሻሉ ቴክኖሎጂዎችን ገዝተው ወደ ማምረቱ መግባት እንደቻሉም ነው የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መረጃ ያመላከተው።

ማሻሻያው በአነስተኛ ደረጃ የሚመረተውን የማእድን ምርት በከፍተኛ መጠን እያሳደገው ሲሆን፤ በተለይ የወርቅ ምርታማነት በከፍተኛ ደረጃ እያደገ ነው። ለዚህም ነው በ2017 በጀት ዓመት ስምንት ነጥብ ስድስት ቶን ወርቅ ለማምረት ታቅዶ፣ ባለፉት ሶስት ወራት ብቻ የዚህን እቅድ 70 በመቶውን ማሳካት የተቻለው።

በተመሳሳይ መልኩ፣ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ትግበራውን ተከትሎ ብሄራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሪ ግብይት አስተዳደር ሥርዓቱ በገበያ እንዲወሰን የወሰደው እርምጃ፤ በተለይ ግብይታቸው ከውጭ ምንዛሪ ጋር ትስስር ላለቸው እንደ ወርቅ ላሉት ምርቶች ግብይት ይዞት የመጣው መልካም እድል ስለመኖሩ አፈጻጸሙ በሚገባ አሳይቷል።

ባለፉት ዓመታት ለብሄራዊ ባንክ ይቀርብ የነበረው የወርቅ ምርት መጠን በከፍተኛ ደረጃ ማሽቆልቆሉ ይታወሳል። ምርቱ ለጥቁር ገበያ ሲሳይ በመሆኑ ሀገር ከምርቱ ማግኘት የነበረባትን ጥቅም ስታጣ ቆይታለች።

ከሕገወጥ ድርጊቱ ጋር በተያያዘ ከዓመታት በፊት ለብሄራዊ ባንክ ይገባ ከነበረው በእጅጉ ያነሰ የወርቅ ምርት ነው ለባንኩ ሲቀርብ የነበረው። አንዳንድ ወርቅ በማምረት ሥራ የሚታወቁ ክልሎችም አመረትን ይሉት የነበረው የወርቅ መጠንም ከቀደሙት ዓመታት የወርቅ ምርታቸው ያንስም ነበር።

ወርቅ አምራቾች ችግሩ የተፈጠረው ለምርቱ ተገቢውን ዋጋ ካለማግኘት ጋር የተያያዘ ስለመሆኑ ሲገልጹ ቆይተዋል፤ በአንጻሩ ብሄራዊ ባንክም ይህን ቅሬታ ለመፍታት ወርቅ ለሚያቀርቡለት አካላት በወርቅ መረከቢያ ዋጋ ላይ በተደጋጋሚ ማሻሻያ ሲያደርግ ነበር። ሆኖም ችግሩ ከጥቁር ገበያ መንሰራፋትም ጋር ጭምር የተያያዘ ነበር፤ ህገወጦቹ የወርቅ ግብይቱን ብቻ ሳይሆን የማምረት ስራውን ጭምር እየተቆጣጠሩ የመጡበት ሁኔታም ተፈጥሮ እንደነበር ይታወሳል።

መንግሥት የሀገርን ጥቅም በእጅጉ የሚጎዳውን ይህን ሕገወጥ ድርጊት ለመቆጣጠር በሀገር ደረጃ ግብረ ኃይል በማቋቋም በሕገወጥ የወርቅ ማምረትና ግብይት ተግባር በተሰማሩ አካላት ላይ ቁጥጥር በማድረግ እርምጃ መውሰድ ውስጥ በመግባቱ፣ በርካታ የውጭ ሀገር ዜጎች እና ኢትዮጵያውያን በቁጥጥር ስር መዋላቸው ይታወቃል።

ይሄም ሕገወጥ ድርጊቱን በተወሰነ ደረጃም ቢሆን መቆጣጠር የተቻለበትን ሁኔታ የፈጠረ ቢሆንም፤ ዘላቂ መፍትሄ ግን መሆን ሳይችል ቆይቷል። በአንዳንድ ክልሎችም ችግሩ በመሠረታዊነት እንዳልተፈታ ሲናገሩ የነበረውም ለዚህ ነው። አሁንም ድረስ ከጸጥታ ችግር ጋር በተያያዘ የወርቅ ማምረቱም ሆነ የግብይቱ ሥራ በሕገወጦች ተጽእኖ ስር የወደቀባቸው አካባቢዎች እንዳሉ እየተጠቆመ ነው።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ተሆኖም ነው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ማድረግ እና ችግሩን በሌላ መንገድ ለመፍታት ወደ ርምጃ የተገባው። መንግሥትም በዚህ መልኩ ርምጃ መውሰድ በመቻሉ ለእዚህ ግዙፍ ችግር ፍቱን መፍትሄ መስጠት ችሏል። የ100 ቀናት ግምገማውም በሚገባ ያመላከተው ይሄንኑ እውነት ነው። በመሆኑም ቀጣዩ ሥራም ይህን ጥሩ አፈጻጸም ዘላቂ ለማድረግ ጠንክሮ መሥራት ሊሆን ይገባል።

ለአብነትም፣ ማእድን ሚኒስቴር ባህላዊ ወርቅ አምራቾች በአነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ወርቅ አምራችነት እንዲሠሩ የፈጠረው ምቹ ሁኔታና ያንን ተከትሎም በወርቅ ምርት ላይ እየመጣ ያለው ለውጥ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረግ ይኖርበታል። ምክንያቱም ጅምር ተግባሩ ከማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ድጋፍ ጋር ተዳምሮ ለብሄራዊ ባንክ የሚገባው የወርቅ መጠን እንዲጨምር ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ነውና።

ማሻሻያው አምራቹንም ሀገርንም በእጅጉ የሚጠቅም እንደመሆኑ ትግበራው በወርቅ ግብይት ላይ ይስተዋል ለነበረው ሕገወጥ ተግባር መፍትሄም ይዞ መጥቷል። ባለፉት ሶስት ወራት ወደ ብሄራዊ ባንክ የገባው ከፍተኛ መጠን ያለው የወርቅ ምርትም ይህንኑ በሚገባ አመላክቷል። ስለዚህ ይህን ውጤታማነት ዘላቂ ለማድረግ ባለፉት ሶስት ወራት በተካሄደው የማሻሻያው ትግበራ የተገኙ ተሞክሮዎችን በማስፋት ለላቀ ውጤታማነት ርብርብ ማድረግ ከሁሉም ባለድርሻዎች የሚጠበቅ ተግባር ነው።


**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## የፋውንዴሽን ያለህ

ግርማ መንግሥቴ

የኢኮኖሚ (ኢኮኖሚያዊ) እኩልነትም ሆነ እኩል ተጠቃሚነት (Equity) መልኩም ሆነ መንገዱ ብዙ ነው። እንደየ ሀገሩ ይለያያል፤ እንደየ መንግሥታቱ ርእዮት ይቀያየራል፤ እንደ አህጉርና ዓለም አቀፍ ሁኔታዎችና ይዞታዎች ልዩነቶች ይስተዋሉበታል። በተለይ፣ እንደየ ሀገራቱ የእድገትና ብልፅግና ደረጃ የፅንሰ ሀሳቡ ገቢራዊነትም በዛው ልክ ዥንጉርጉር ነው። አንዳንዱ ጋ ሞልቷል፤ አንዳንዱ ጋ ሽታውም የለም።

ሀገራት (ቱጃር ግለሰቦችን ጨምሮ) ከዜጎቻቸውም አልፈው ሌሎችን "ተጠቃሚ" የሚያደርጉባቸው፤ ተጠቃሚነታቸውንም የሚያረጋግጡባቸው፤ ሀገር ያፈራው ኢኮኖሚ ደሀው ዘንድ ሳይቀር እንዲደርስ የሚያደርጉባቸው በተቋማት የተደገፉ የአሰራር ዘዴዎች ያሏቸው ሲሆን፤ አንዱም ፋውንዴሽን ነው።

ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ቱጃሮች ጥቂት ግለሰቦች አለያም መንግሥት ነው። በሶሻሊስት ሀገራት ዘንድ የሀገሪቱ ሀብት በመንግሥታቱ ስር ነው። በሌላ በኩል በካፒታሊስት ሀገራት ውስጥ (በአሜሪካኖቹ በአንድ ወቅት አንድ በመቶ የሆኑትን ቱጃሮችና መንግሥት ለእነሱ የሚያደርገውን ድጋፍ በመቃወም "እኛ 99 በመቶ ነን" እንዳሉት) ደግሞ የሀገሪቱ ሀብት በጥቂቶች መዳፍ ውስጥ ነው። በመካከል ላይ ያለው (ቅይጥ ኢኮኖሚ?) ብዙም ገፍቶ በመውጣት ከፍትሀዊ የሀብት ክፍፍልም ሆነ እኩልነት ጋር ትከሻ ለትከሻ ቆሞ ሲሄድ አይታይም። አንዳንዴ እንደውም ከንድፈ - ሀሳብ ደረጃ እንኳን የዘለለ አይመስልም።

ይህን ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል (የዜጎች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት) በተመለከተ በርካታ ሀገራት ብዙ ሥርዓቶችን (ሲስተምስ)ና አሰራሮችን ዘርግተው ዜጎችን ተጠቃሚ ሲያደርጉ ይታያሉ። ከእነዚህ ተቋማዊ አሰራሮች አንዱ ደግሞ ፋውንዴሽን ማቋቋም ነው። ከዚህ አኳያ፣ ከሀገራቸውም አልፈው እዚህ እኛ ድረስ እጃቸውን የዘረጉ በርካቶች ናቸው። ከእነዚህም አንዱ በተለይ በአፍሪካ የምግብ ዋስትና ላይ አተኩሮ የሚንቀሳቀሰው የ"ቢል እና ሚሊንዳ ጌትስ ፋውንዴሽን" (ፊላንትሮፒ) ነው።

የዓለማችን ቁጥር 1 ቱጃሩ ቢል ጌት በግብርናው ዘርፍ ላይ ከማተኮር አኳያ እጃቸው ረዘም ይበል እንጂ፣ በፋውንዴሽናቸው አማካኝነት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ እጃቸውን በመዘርጋት ይታወቃሉ። ለማሳያ ያህል እሳቸውን ከጠቀስን ወደ ሀገራችን በመመለስ "ፋውንዴሽን" ያለበትን ሁኔታ እንመልከት።

በሀገራችን ፋውንዴሽኖች "አሉ" ብሎ መነሳት መቀለድ ነው የሚሆነው። በመሆኑም "የሉም" ብሎ ከመደምደምም በፊት ቢያንስ በሃሳብ ደረጃ ቦግ/እልም ይሉ የነበሩትን እንጥቀሳቸውና ወደ "መሆን ያለበት" ሃሳባችን እንመለስ።

በሀገራችን አክሊሉ ለማ ፋውንዴሽን (ከነበሩት ሁሉ እሱ ነው ነፍሱ ያለው)፣ በአሉ ግርማ ፋውንዴሽን፣ መለስ ዜናዊ ፋውንዴሽን ወዘተ ተብሎ "የመሰረት ድንጋይ" ከመጣል ያልተናነሰ የማስተዋወቂያ ፕሮግራሞች ይካሄዳሉ። ንግግሮች ይደመጣሉ። ጭብጨባዎች ይስተጋባሉ ፨ ፨ ፨ ከዛ ወደ ቤት። ከዛ ፨ ፨ ፨ ዝም፣ ጭጭ ፨ ፨ ፨ በቃ።

እንደ ተነገረን ከሆነ፣ ምናልባት በቅርብ ጊዜ ውስጥና የመጨረሻው (የቅርቡ) ፋውንዴሽን "የፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ፋውንዴሽን" ነው፤ ያለበትን ሁኔታ ባናውቅም እነ ፕሮፌሰር ብርሀኑ ነጋን ጠይቆ አንድ ነገር የሚለን እስኪመጣ ድረስ ይህንን ፋውንዴሽን እንዲህ ነው፣ እንዲያ ነው ...ከማለት እንቆጠባለን።

ሥርዓት ባለው ሁኔታ፣ ሕግና ደንብን በተከተለ አካሄድ፣ ሰዎችን (ዜጎችን) ሊጠቅም በሚችል መልኩ የሀገርን ኢኮኖሚያዊ እድገት ሊደግፍ (ሊያፋጥን) በሚችል አሰራር ከሚደረጉ ተቋማዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች መካከል አንዱ በእውቅ ሰዎች ስም የሚቋቋም (ወይም፣ ራሳቸው በሕይወት እያሉ የሚያቋቁሙት) ፋውንዴሽን ነው።

በሀገራችን ፋውንዴሽን እና ምንነቱ በአግባቡ ይታወቃል ለማለት ድፍረትን ይጠይቃል። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ እከሌ ደግ ነው፣ ገንዘብ ይሰጣል፤ እንትና ንፉግ ነው፣ ምንም አይደማውም (ለምሳሌ፣ ጥያቄው "ፋውንዴሽን አቋቁሟል ወይስ አላቋቋመም?" (ያለ ማቋቋም መብቱ እንዳለ ሆኖ) መሆን ሲገባው፣ ኃይሌ ገብረሥላሴን በሬዲዮ ሳይቀር ሲወቅሱ የነበሩ ሰዎች እንዳሉ እየታዘብን ነው።

**ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል (የዜጎች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት) በተመለከተ በርካታ ሀገራት ብዙ ሥርዓቶችን (ሲስተምስ)ና አሰራሮችን ዘርግተው ዜጎችን ተጠቃሚ ሲያደርጉ ይታያሉ። ከእነዚህ ተቋማዊ አሰራሮች አንዱ ደግሞ ፋውንዴሽን ማቋቋም ነው**

እከሌ ይሄንን ያህል ሚሊዮን ለእንትና ሰጠው/ጣት፤ መኪና ገዝቶ ሰጣት/ጠው ፨ ፨ ፨ እና የመሳሰሉ አስተያየቶች ብዙ ጊዜ ከተማውን ሲያጨናንቁ ("ቶክ ኦፍ ዘ ታውን" ሲሆኑ) ይስተዋላል። እውነቱ ግን፣ ከግል ዝና በዘለለ ይህ ሁሉ የ"አባ መስጠት" ተፍ ተፍ ሀገርንም ሆነ ማህበረሰብን ሊለውጥ የሚችል ምንም ረብ የሌለው ተግባር መሆኑ ነው።

በምትኩ፣ እንትና ፋውንዴሽን አቋቋመ፤ እከሌ ወጣቶች በነፃ ስልጠና የሚያገኙበት ማሰልጠኛ ማእከል ገነባ፤ እንትን ተቋም ወጣቶችን አደራጅቶና አሰልጥኖ ወደ ስራ አሰማራ፤ እነ እከሌ ማህበረሰቡ በነፃ የፍትህ አገልግሎት የሚያገኝበትን ተቋም አቋቋሙ፤ እንትና ባንክ "ታለንት" ያላቸውን ወጣቶች አሰባስቦ፣ መልምሎና አሰልጥኖ፣ ፕሮጀክቶችን ቀርፆ፣ በጀትና አማካሪ መድቦ ወደ ስራ እንዲገቡ አደረገ (ይህ በሌላው ዓለም ባሉ የግል ባንኮች እጅግ ቀላሉና ሁሌም የሚደረግ ነው) ፨ ፨ ፨ ወዘተ ሲባል አይሰማም። ታዲያ ካልተሰማ እንዴት አድርጎ "በሀገራችን ፋውንዴሽን እና ምንነቱ በአግባቡ ይታወቃል" ማለት የሚቻለው?

እንደሚታወቀው፣ እኛ ሀገር "በደንብ" እንደሚታወቀው "አክሲዎን" እንጂ ሰብአዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋም አይደለም። እኛ ሀገር በሚገባ ስሙ የሚጠራና ተገቢውን እውቅና የሚያገኘው በየመንገዱ የሚመነዝርና ሻሞ የሚል እንጂ፣ እንደ አበበች ጎበና ያለው ለመታወቅ ምእተ ዓመትን ይፈጅበታል። የቀዳማዊት እመቤት ጽህፈት ቤት የበርካታ ትምህርት ተቋማት ግንባታ ብዙም እየተወራለት ያለ ሰብአዊ ተግባር አይደለም። እኛ ሀገር ዝናው የሚናኘው መሸታ ቤት የከፈተ እንጂ ሰው ተኮር እንቅስቃሴን ያደረገ አይደለም። የእኛ ሀገር ጭብጨባ ለሚናገር እንጂ ለሚሰራ ሰው አይደለም፤ ሆኖም አያውቅም። ብዙ ማለት ይቻላል።

በዚህ ጽሑፍ አማካኝነት ለማለት የተፈለገው "በሌላው ሀገር የተትረፈረፈው ፋውንዴሽን እዚህ፣ እኛ ሀገር ለምን ደብዛው ጠፋ?" የሚለው ነው። የአንድ ሀገር ኢኮኖሚ፣ በጥቂቶች የተያዘ ኢኮኖሚ፣ በሙስናም ይሁን ሌላ የተግበሰበሰ ኢኮኖሚ ወዘተርፈ ወደ ደሀው፣ በገዛ ሀገሩ ያጣ የነጣው ክፍል የሚሄደው ፋውንዴሽንና እሱን በመሳሰሉ ተቋማት አማካኝነት መሆኑ ይታወቃል።

በግብረ ሰናይ ድርጅቶች አማካኝነት ነፍስ ከሞት እንደሚተርፍ ሁሌም የሚታይ እውነት ነው። ይሁን እንጂ፣ ይሄ ሁሉ "የሕፃናት ፨ ፨ ፨" ባለበት ከተማ፤ ይሄ ሁሉ "የሴቶች ፨ ፨ ፨" ባለበት ሀገር፤ ይሄ ሁሉ "የአረጋዊያን ፨ ፨ ፨" (መቄዶኒያን አይመለከትም) ባለበት ምድር መሬት ላይ ምንም አለመታየቱ እንቆቅልሽ መሆኑ እንዳለ ሆኖ፤ ምናልባት የሀገራችን ቅን ባለሀብቶች በሚያቋቁሟቸው ፋውንዴሽኖች አማካኝነት ወደ ፊት (በቅርቡ) ለውጦችን እንመልከት፤ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍሉም ተግባራዊ፣ ሰብአዊ ድጋፉም እውን ሆኖ የምናይበት ጊዜ ይመጣል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

## ነፃ ሃሳብ

# የአዲስ አበባን አለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ለማሳደግ

በጋዜጠኛና ሲኒየር የኮሙኒኬሽን ባለሙያ ሳንዱዘር አሥራት

የልማት ተነሺዎችን ጉዳይ ፈጽሞ ባልተገባ፤ ባልተደረገና እየተፈጸመ ካለው ነባራዊ እውነት በተቃራኒ በማጮህ አጀንዳውን ለፖለቲካ ትርፍ እንደ መጫወቻ ካርድ መጠቀምን ጨምሮ የማህበራዊ ሚዲያ መሸቀያ ማድረግ ዜጎች ላይ ከሚያስከትለው የሥነ ልቦና ቀውስ ውጭ አንድም የሚያመጣው መልካም ነገር ይኖራል ተብሎ አይታሰብም።

በሀገርም ይሁን በከተማ ደረጃ፤ የጋራ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ያስችላሉ ተብለው የተለዩ ልዩ ልዩ ተግባራዊ ርምጃዎች በሚወሰዱበት ወቅት፤ ለዘላቂ የሀገር ግንባታ የሚሆኑ ተግባራትን በጋራ መፈጸምና የድርሻን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት መቻል ከዳበረ የሀገር ፍቅር ቀናኢ አመለካከት የሚመነጭ ነው ።

የቱንም ዓይነት ስም የተሰጠው የፖለቲካ ድርጅት፤ የግለሰብ አቋምም ይሁን በምንም ጉዳይ ላይ ያለ አስተሳሰብ በጊዜ ሂደት የሚሻርና የሚለወጥ ነው ፤ በሚያንጽ አግባብ ለሀገር ግንባታ የበኩልን አስተዋጽኦ ማበርከት መቻል ደግሞ ለትውልድም ለሀገርም በታማኝነት የሚቀመጥ ዐሻራ ሆኖ ስምን ከመቃብር በላይ እንዲውል የሚደረግ እውነታ ነው።

ለዚህም ኢትዮጵያውያን አባቶቻችንና ቅድም አያቶቻችን ልዩነቶችን ተሻግረው ሀገረ መንግሥትን በማጽናትና ጠብቀው በማቆየት እንዲሁም ለሀገር ግንባታ የሚበጅ በጎ ዐሻራን በአንድነት በማኖር ህያው ምሳሌ ሆነው ዛሬም ድረስ የሚታወሱ ናቸው።በሀገር ጉዳይ ያላቸውን አንድነትና ምሳሌነት መከተል ስለ ሀገር ፍቅር በቅንነት የሚከፈል ዋጋ እንጂ ለየትኛውም ስብስብና ግለሰብ ጥብቅና እንደመቆም ተደርጎ የሚወሰድ አይደለም።

ከዚህም ጋር ተያይዞ በእጅጉ ዘግይቶም ቢሆን መዲናችን አዲስ አበባ፤ የሁላችንንም በጎ ዐሻራ የሚጠይቅ የኮሪደር ልማትን ያካተተ የስማርት ስቲ የከተማ ልማት ፕሮግራምን ተግባራዊ እያደረገች ትገኛለች። በልዩ ልዩ ምክንያቶች ከአንድ ምዓተ-ዓመት ለሚበልጥ ጊዜ፤ በአዝጋሚ የለውጥ ሂደት ደረጃዋን በማይመጥን ብሎም የነዋሪዎቿን ሕይወትና የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ በሚያከብድ ውስብስብ የመሠረተ-ልማት ችግር ተይዛ ቆይታለች።

ችግሩ ፈጽሞ ለሚቀጥለው ትውልድ መሻገር የሌለበት አፋጣኝ የማስተካከያና የእርምት ርምጃ ሊወሰድበት የሚገባ ተግባር ሆኖ በበርካቶች ሲጠየቅም/ ሲጠበቅ የነበረ ጉዳይ ነው።ለዚህም በወርሀ መጋቢት 2010 ዓ.ም፤ የተደረገውን የመንግሥትና የሥርዓት ለውጥ ተከትሎ በምርጫ ወቅት፤ ከተማዋን አስፈላጊ መሠረተ-ልማቶችን በመዘርጋት በሚፈለገው አግባብና ልክ ለማደስ በመንግሥት ደረጃ ቃል የተገባ መሆኑም ይታወሳል።

አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ርእሰ ከተማ ፣ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ ከመሆኗም ባሻገር ከአሜሪካ ኒዮርክና ከሲዊዘርላንዷ ጄኔቫ በመቀጠል ሦስተኛ፤ ልዩ ልዩ ዓለም አቀፋዊ ውሳኔዎች የሚተላለፉባት የዲፕሎማሲ ማዕከል ሆና አገልግሎት እየሰጠች ትገኛለች።

ይህም ሆኖ ግን ከተማዋ በመንግሥታት የለውጥ ሂደት ዓለም አቀፋዊ የዲፕሎማሲ ማዕከልነቷን ጨምሮ የነዋሪዎቿን አዳጊ ፍላጎቶች ታሳቢ ባደረገ አኳኋን መሠረተ ልማቶቿ በሚፈለገው ልክና አግባብ ባለቤት አግኝተው ሳይበጅላት ኖሯል።ችግሩ በተመሳሳይ መልኩ ለሚቀጥለው ትውልድ መሻገር የሌለበት በመሆኑ፣ የአሁኑ ትውልድ ችግሩን በልኩ ተረድቶ ደፋር የእርምት ርምጃዎችን መውሰድ ላይ ይገኛል።

በዚህም ከአንድ ክፍለ ዘመን ለሚበልጥ ጊዜ እያለፈች ካለችበት ዝግመታዊ የከተሜነት የለውጥ ሂደት በተቃራኒ፤ ባለፉት ስድስት የለውጥ ዓመታት ፈጣንና መጪውን ትውልድ ታሳቢ ያደረገ ዘመን ተሻጋሪ ማዘጋጃ ቤታዊ ዓለም አቀፍ መስፈርትና ተሞክሮዎችን በተከተለ አግባብ በጥራት በ24/7 የሥራ ባሕል መሻሻል መርህ እያከናወነ ይገኛል።

በከተማዋ ተግባራዊ እየተደረገ ያለውን የኮሪደር ልማት ሥራን ጨምሮ፤ በሌሎችም ከለውጡ ማግስት አንስቶ 24/7 በሚል አዲስ የሥራ ባሕል፤ ለሕዝብ የላቀ ጠቀሜታ ያላቸው የልማት ሥራዎች በአዋጭነት ጥናት እየተለዩ ተገንብተው ለሕዝባዊ አገልግሎት እንዲውሉ እየተደረጉ ነው።ይህም በስፋት በከተማዋ ሁሉም አካባቢዎች ለማለት በሚያስደፍር መልኩ ይስተዋላል።

በመሀል አዲስ አበባ 50 ዓመት ያለፋቸው የጭቃ ቤቶች፣ ያለ አንዳች እድሳትና ማሻሻያ፣ በዕድሜ ብዛት እየወላለቁና እየዛጉ እስከ መቼ ሊቀጥሉ ይችላሉ? ከተማዋ ገና በምትቆረቆርበት ወቅት ተዘርግተው የነበሩ የመሠረተ ልማቶች ጉዳይስ? ዘመናዊ የከተማ ማዘጋጃ ቤት ሥርዓት ከመዘርጋት አኳያ ያለው እውነታስ?

ከተማዋ እንድታድግ እና እንድትዘምን፣ የነዋሪዎች የኑሮ ደረጃና የሥራ ሁኔታ እንዲሻሻል ከተፈለገ የኮሪደር ልማትን ጨምሮ ዘመን የደረሰባቸውን የስማርት ሲቲ ፕሮግራሞች ደረጃ በደረጃ ተግባራዊ ከማድረግ በስተቀር ሌላ ሁለተኛ አማራጭ ይኖረን ይሆን?

አሁን ላይ ካለው ተጨባጭ የከተማዋ እውነታ አኳያ ሁለተኛ አማራጭ እንደማይኖረን በመንግሥት ደረጃ ታምኖበት ወደ ሥራ ተገብቷል፣ እስካሁን ባለው አካሄድም ሁኔታዎች ተስፋ ሰጭ ስለመሆናቸው በከተማዋ በጥራት እና በፍጥነት የሚገነቡ መሠረተ ልማቶች እና የከተማ እድሳቶች ማሳያ ናቸው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በተገባደደው የ2016 በጀት ዓመት በስማርት ሲቲ የከተማ ልማት ፕሮግራሞች ማሕቀፍ ተግባራዊ መደረግ የጀመረው የኮሪደር ልማት ፤ በሁሉም ረገድ የሚገለጽ ዘላቂ ዕድገትና የነዋሪውን አዳጊ ፍላጎቶች ማዕከል በሚያደርግ አኳኋን የልማት ዕቅዶችን ደረጃ በደረጃ ተግባራዊ ማድረግ እያስቻለ ነው።

የኮሪደር ልማት ሥራው ዋነኛ ዓላማ ከተማዋ በሁሉም ረገድ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን እንድታሟላ ማስቻልና ለነዋሪዎቿ ምቹ የመኖሪያ ከባቢ መፈጠርን የሚያረጋግጡ መሠረተ ልማቶች እንዲኖሯት ማድረግ ነው።በዚሁ አግባብ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን ከተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ያዋሀዱ ሥራዎች በስፋት እየተከናወኑ ነው።

የአዲስ አበባን የኮሪደር ልማት ሥራ በሚመለከት በሀገር ውስጥ የሌሉ አካላት ከተማ አስተዳደሩ በሁለቱም ዙሮች ለልማቱ ተነሽዎች እያቀረበ ካለው ካሳ ማካካሻና የማቋቋሚያ ሥርዓትን በሚቃረን አኳኋን፤ ነዋሪዎች ከአካባቢያቸው ያለ አንዳች ካሳና ማካካሻ እየተነሱ ናቸው።የሚል ሀሰተኛ መረጃ እያሰራጩ መሆናቸው ሲታይ ደግሞ የልማቱን ዓላማ ካለመረዳት አሊያም በተለመደው አግባብ ሥራዎችን ለማጣጣል ታስቦ የሚደረግ መሠረተ-ቢስ ውንጀላ ይመስላል።

በመንግሥት የሚከናወኑ የከተማ ልማት ሥራዎችን ጨምሮ ሌሎችንም የመልካም አስተዳደር ሥራዎች፤ ካለ አንዳች ተጨባጭ ማስረጃ በማጣጣል ከማህበራዊ ሚዲያዎች ለሚገኝ ሸርፍራፊ ገንዘብ ቀኑን ሙሉ ሲዋሹ የሚውሉ አካላትን ጨምሮ ፖለቲካዊ ትርፍን ከአማራጭ የፖለቲካ ሃሳብ ውጭ ጊዜ ባለፈበት የማጣጣል አባዜ የሚያገኙ የሚመስላቸው አካላትም ከወዲሁ መታረም ቢችሉ መልካም ይሆናል።

የጩኸቱ መበርከት በቂ መረጃ ለሌለው ሰው ለተነሺዎች በመቆርቆር የሚደረግ ሊመስል ይችላል። እውነታው ግን እንደሱ አይደለም። ጩኸቱ ከማህበራዊ ሚዲዎች የሚገኝ ሽርፍራፊ ገንዘብና የፖለቲካ ትርፍን ለማግኘት የሚደረግ ጥረት አንድ አካል ነው።ለዚህ ደግሞ ተነሺዎች በተለያዩ ወቅቶች በራሳቸው አንደበት የሚናገሩትን በቀና መንፈስ መስማት በቂ ነው።

ለሕዝብና ለሀገር የመቆረቆር ቅን ልቦና ያለው አካል በሚቻለው ሁሉ ዜጎችን በማቋቋም ሂደት ችግሮች እንዳያጋጥሙ ማድረግ፤ መንግሥት በየደረጃው ከሚያከናውናቸው የማካካሻ ተግባራት በተጓዳኝ በቡድንም ይሁን በተናጠል ቀርቦ የድርሻን ማህበራዊ ኃላፊነት መወጣት መቻል ፤ ሌሎችን የሚያስተምር የስልጡን ዜጋ መገለጫ መሆኑ እሙን ነው።

ከተማ አስተዳደሩ ለኮሪደር ልማት ተነሽዎች ብቻ የሚውል በጀት አስቀድሞ በማዘጋጀት ካሳ ተለዋጭ/ምትክ መሬት በየደረጃው ላሉ የንግድ ሥራዎች የሚሆኑ የመሥሪያ ቦታዎችን ጨምሮ ለከተማ አኗኗር የሚመጥኑ ቤቶችን በማዘጋጀት የልማቱ ተነሽዎችን በዚሁ አግባብ እያስተናገዱ ነው፤ ይህ በአብዛኛው የከተማዋ ነዋሪ ዘንድ ይታወቃል።

ሁለተኛው ዙር የከተማዋ የኮሪደር ልማት ሥራም ቢሆን እንደ መዳረሻዎቹ ስፋት ሁሉ በመጀመሪያ ዙር ከነበረው በሦስት ዕጥፍ የሚበልጥ ነው።እንደ አጠቃላይ የሁለተኛው ዙር የልማት ሥራው ስፋት በመጀመሪያው ዙር ለ50ሺህ ሠራተኞች የሥራ ዕድል ፈጥሮ ከነበረው በላይ ለበርካታ የእንጨት፣ የብረታ ብረት፣ የኤሌክትሪክ፣ የኮንክሪት፣ የአስፋልት ንጣፍና ግንበኞች የሥራ ዕድል የሚፈጥር ነው።ይህም ወደ ሥራ ተቋራጭነት እስኪሸጋገሩ ድረስ አቅም እንዲፈጠርላቸው የሚያስችላቸው ይሆናልም ተብሎ ይጠበቃል።

በርካታ የከተማዋ የውስጥ ለውስጥ አካባቢዎች የተፋፈጉ፣ ለኑሮና ለሥራ፣ ለእንቅስቃሴና ለጤናም የማያመቹ አልፎም የስጋት ቀጠና መሆናቸው እምቅ አቅማቸው እንዳይታይ ከማድረጉም በላይ ዕድገት እንዳያሳዩ አምክኗቸዋልም።ይህንን ተከትሎ የዜጎች የማደግ ፍላጎትና ኑሯቸውን የማሻሻል ጥረትም ተከርችም የተቆለፈበት እንዲሆን አድርጓልም።

የከተማዋ የኮሪደር ልማት ለዜጎች ይዞት በመጣው መልካም ዕድል ሳቢያ፤ እጅግ የተጎሳቆሉና ለመኖር ምቹ ያልሆኑ መኖሪያ ቤቶችን ጨምሮ የንግድ ቤቶች ውስጥ የነበሩ በርካታ የልማት ተነሺ ነዋሪዎች ምቹ የመኖሪያ እና መሥሪያ ቦታ እንዲያገኙም አስችሏቸዋል። በአገልግሎትና በአቅርቦት ሥራ ላይ የተሰማሩ ብዙሃን የንግዱ ማህበረሰብ አካላት በተመሳሳይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ፤ በልማቱ ሳቢያ የተፈጠረው ሰፊ የገበያ ትስስር ተጠቃሚ ሆነዋል።

የአዲስ አበባ ከተማን፣ ዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲያዊ ተቀባይነትና የነዋሪዎቿን በሁሉም ረገድ የሚገለጽ አዳጊ ፍላጎቶች በሚፈለገው ልክና ፍጥነት ማረጋገጥ እንዲቻል፤ የተጀመሩ ጥረቶች አሁን ላይ እያስመዘገቡት ካለው ስኬት አኳያ፤ ከተማዋ በቅርብ ዓመታት ውስጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚኖራት ተወዳዳሪነት ትርጉም ያለው እንደሚሆን ይታመናል።

**አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ርእሰ ከተማ ፣ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ ከመሆኗም ባሻገር ከአሜሪካ ኒዮርክና ከሲዊዘርላንዷ ጄኔቫ በመቀጠል ሦስተኛ፤ ልዩ ልዩ ዓለም አቀፋዊ ውሳኔዎች የሚተላለፉባት የዲፕሎማሲ ማዕከል ሆና አገልግሎት እየሰጠች ትገኛለች**

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የታዳጊዎችን የፈጠራ ክህሎት የሚያጎለብተው ስቲም ማዕከል

ዘመነ ቴክኖሎጂ ተማሪዎች በሳይንስና በሒሳብ ትምህርቶች ጎልብተው የህብረተሰቡን ችግር በሚፈቱ የፈጠራ ሥራዎች ሥራ ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች መፍጠርን ይጠይቃል። ለዚህም ነው በሳይንስ፣ በሒሳብ፣ በኢንጂነሪግ እና በሮቦቲክ ላይ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ እንደ ስቲም ፓወር አይነት ድርጅቶች ማዕከላትን በማቋቋም ተማሪዎችን በማሰልጠን ወጣቶች ወደ ቴክኖሎጂው ጠልቀው እንዲገቡ ምቹ ሁኔታ እየፈጠሩ ናቸው።

የስቲም ፓወር በኢትዮጵያም በሀገሪቱ ለሚገኙ ለ65 የስቲም ፓውር ማዕከላት ድጋፍ ያደርጋል። በእነዚህ ማዕከላት ከመጀመሪያ ደረጃና ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተወጣጡ ተማሪዎች በሮቦቲክስ፣ በኤሌክትሮኒክስ፣ በኮምፒዩተር ሳይንስና በሌሎችም መሰረታዊ ሳይንስ በሚባሉት በሂሳብ፣ በፊዚክስና በሌሎችም ዘርፎች ይሰለጥናሉ።

በስቲም ፓወር ከተቋቋሙ ማዕከላት መካከል የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ማዕከል አንዱ ነው። ይህ ማዕከል ከተቋቋመበት ጀምሮ በርካታ ተማሪዎች እያሰለጠ ይገኛል።


የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ስቲም ማዕከል አስተባባሪ አቶ አለምሰገድ ሞረዳ እንደሚለው፤ በዩኒቨርሲቲው ሥር የሚገኘው ስቲም ማዕከል በ2008 ዓ.ም የተመሠረተ ነው። ማዕከሉ የተለያዩ ላብራቶሪዎች እና የራሱ የሳይንስ ሙዚየምም አለው። አሁን ስልጠናዎችን ይሰጣል። ከስልጠናዎቹ መካከል ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት /ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ላሉ/ ተማሪዎች የመጀመሪያ ዙር ስልጠና ይሰጣል። ይህ ስልጠና የሚያካትታቸው የኬሚስትሪ፣ የሒሳብና የፊዚክስ ትምህርቶችን ሲሆን፣ በንድፈ ሃሳብ ብቻ ሳይሆን በተግባርም ጭምር በላብራቶሪ የተለያዩ ሙከራዎች እንዲያደርጉ በማስቻል የሚሰጥም ነው።

የመጀመሪያ ዙር ሰልጣኞች ስልጠናውን በበጋው መርሃ ግብር ለሁለት ወራት እንዲወስዱ ይደረጋል። ስልጠናውን ከወሰዱ ከሁለት ወራት በኋላም ለመመዘኛ ፈተና ይቀመጣሉ። ፈተናውን ካለፉ ወደ ሁለተኛ ዙር ስልጠና እንዲገቡ ይደረጋል። በሁለተኛው ዙርም እንዲሁ አራት የስቲም ፕሮጀክት የትምህርት ዓይነቶችን ይማራሉ። ከእነዚህ ውስጥም ኤሌክትሮኒክስ፣ ሮቦቶችንና የተለያዩ ቴክኖሎጂዎች መሥራት የሚያስችላቸው «ኢንቤድድ ሲስተም» እንዲሁም ፕሮግራሚንግ እና ሶሊድ ዋርክ ናቸው። ሶሊድ ዋርክ የኮድ ሶፍትዌር አይነት ሲሆን፣ ተማሪዎቹ ሥራቸውን በራሳቸው ዲዛይን እንዲያደርጉ ያስችላል። ይህ ሶፍትዌር ተማሪዎቹ የሚሰሯቸውን ሮቦቶች እና ሌሎችንም ቴክኖሎጂዎች ኮምፒዩተር ላይ መፍጠርና ራሳቸው በቀላሉ ዲዛይን እንዲያደርጉ ያስችላል።

አራቱን ኮርሶች ለመውሰድ ሁለት ወር ያህል ይፈጃል። ሁለተኛውን ዙር ካጠናቀቁ በኋላ ፈተና ይሰጣቸዋል። ፈተናውን ካለፉ ወደ መጨረሻ ዙር ይሸጋገራሉ። የመጨረሻው ወይም ሦስተኛው ዙር ፕሮጀክት የሚሰራበት ነው። ስለሮቦቲክስ የሚሰለጥኑበት እና ኢንጂነሪንግ ወይም ስቲም ፕሮጀክት የሚሰሩበት ነው። ተማሪዎቹ ሦስተኛው ዙር ላይ ሲደርሱ በሁለት ቡድን ተከፍለው የመጀመሪያ «ፕሮጀክት ኤ» እና ሁለተኛው «ፕሮጀክት ቢ» ተብለው ይሰየማሉ።

የመጀመሪያው ቡድን በ‹ፕሮጀክት «ኤ» ያሉት ለሁለት ወር በሮቦቲክ ላይ ስልጠና ይሰጣቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ ሚኒ የሚባል ፕሮጀክትም ይሰራሉ። ይህንን ፕሮጀክት እንዲሰሩ የሚደረግበት ዋና ዓላማ በቡድን ሆነው ስለሚሰሩ ከመጀመሪያው ዙር እስከ ሁለተኛው ዙር የተከታተሏቸውን የስቲም ፕሮጀክቶች ተግባራዊ አድርገው ቴክኖሎጂ እንዲሰሩ ለማስቻል ነው ሲል አቶ አለምሰገድ ያብራራል።

ተማሪዎቹ ይህንን ቴክኖሎጂ እንዲሰሩ መደረጉ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው አስተባባሪው አቶ አለምሰገድ ጠቅሶ፤ ወርክሾፕ ገብተው ቁሳቁስን በሚጠቀሙበት ወቅት እውቀታቸውን እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል ይላል። ለአብነትም በወርክሾፑ መቁረጫ፣ መበየዳ እና መብሻ ማሽኖች መጠቀም እንደሚለማመዱበት መሆኑን ጠቅሶ፣ በራሳቸው መሥራት እንዲችሉ ምቹ



አሣ እርባታ ላይ የሚያገለግል ሮቦት

ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል ብሏል። በኤሌክትሮኒክስ የሙከራ ክፍል እንዲሁ ከኤሌክትሮኒክስ ጋር የተያያዙ ቁሳቁስ እየተጠቀሙ በራሳቸው ስለሚሰሩ የስቲም ትምህርቶች በይበልጥ ወደ ተግባር የሚለወጡበትና በብዛት ክህሎት የሚያዳብሩበት እንደሆነ ይገልጻል።

አቶ አለምሰገድ እንደሚለው፤ ተማሪዎቹ በዚህ ዙር የሰሯቸውን ሥራዎች ከሁለት ወር በኋላ ለውድድር አቅርበው ይወዳደሩባቸዋል፤ የተሻለ የሰራ ቡድንም ይሸለማል። እነዚህ ተማሪዎች ወደ ሶስተኛ ዙር ሲገቡ ለሁለት በቡድን የተከፈሉት የፕሮጀክት «ኤ» ተማሪዎች ናቸው።

እነዚሁ ተማሪዎች ቀጥሎም በዚሁ ሦስተኛ ዙር ላይ ፕሮጀክት «ቢ» ወይም አድንቫንስድ ፕሮጀክት ቡድን ተብለው እንዲገቡ ይደረጋል። እነዚህ በየዓመቱ በኅዳር ወር በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚካሄደው የሮቦቲክና ኢንጂነሪንግ ውድድር የሚቀርቡ ናቸው፤ በዓለም አቀፉ የሮቦቲክ ውድድር ላይ የሚሳተፉም ይሆናሉ። ዘንድሮ በቱርክ በሚካሄደው ዓለም አቀፍ ሮቦት ኦሎምፒያድ ውድድር ኢትዮጵያ ለመወከል በተዘጋጀ ውድድር ላይ ተሳታፊ ሆነዋል።

ስቲም ማዕከሉ በቅርብ ጊዜ የልጆች የሳይንስ ሙከራ (ኪድስ ሳይንስ ኤክስፐርመንት) የተሰኘ ፕሮግራም ማካሄድ ጀምሯል ሲሉ አቶ አለምሰገድ ጠቁመዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ በዚህ ፕሮግራም ለሰባተኛ ክፍል እና ለስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በተለየ መልኩ ፊዚክስ ላይ ትኩረት ያደረጉ ስልጠናዎች ይሰጣሉ። ፕሮግራሙ በክረምት መርሃ ግብር የሚሰጥ ሲሆን፣ ከተጀመረ በኋላ ውጤታማ መሆኑን መመልከት ተችሏል።

«ስልጠናው ልጆቹን በሚመጥን መልኩ ስለሚሰጥ እነሱም በጣም ተቀብለውታል። በየጊዜው እየፈተሽን ማሻሻያዎችን እናደርጋለን፤ ከዚሀም በኋላ ኮርሶቹ ታይተው ሥርዓተ ትምህርቱ በደንብ ተጠንቶ እነርሱን በሚመጥን መልኩ ተዘጋጅቶ ስልጠናው ይቀጥላል» ሲል አቶ አለምሰገድ ተናግሯል።

ማዕከሉ ከዚህ ሌላ እሴት ጭምራ የተሰኘ ላብራቶሪም እንዳለው ጠቅሶ፣ በዚህ ላብራቶሪ የሳሙና፣ የዘይት እና የወረቀት አሰራር ስልጠናዎች እንደሚሰጡ አመልክቷል። ባዮ መካኒክስ የተሰኘ ላብራቶሪም እንዳለው በማንሳት፤ በዚህም ተማሪዎቹ ለአንድ ወር ያህል ስልጠና እንዲያገኙ እንደሚያደርግ አስታውቋል።

ማዕከሉ ለተማሪዎች ከሚሰጠው አገልግሎት ባሻገር ሌላ ተጨማሪ ስልጠና ለመምህራን እንደሚሰጥ አስተባባሪው አስታውቋል። ማዕከሉ ተማሪዎችን ከየትምህርት ቤቱ ስለሚሰበሰብ እነዚህ ተማሪዎች የተመረጡባቸው ትምህርት ቤቶች መምህራን ተማሪዎቻቸው ስለሚወስዱት ስልጠና ግንዛቤ ኖሯቸው ተማሪዎቹን ወደ ስልጠና ማዕከል እንዲልኩና እንዲተባበሩ የሚያስችል ስቲም የመምህራን ስልጠና (ስቲም ቲቸር ትሬንግ) እንዲኖር መደረጉን ያስረዳል።

«በዚህ ፕሮግራም ከየትምህርት ቤቶቹ የሳይንስ መምህራን በመምረጥ ስልጠና እንሰጣለን፤ እያንዳንዱ ስልጠና ለአንድ ሳምንት ያህል ይሰጣል፤ የኬሚስትሪ፣ የሒሳብ፣ የፊዚክስ፣ የኤሌክትሮኒክስና ፕሮግራሚንግ ትምህርቶች በስልጠናው ይሰጣሉ» ሲል አስታውቋል።

አቶ አለምሰገድ እንዳለው፤ የዩኒቨርሲቲው ማዕከል በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ስር የሚገኝ እንደመሆኑ፣ በዚህ ክፍለ ከተማ ለሚገኙ ተማሪዎች ቅድሚያ እድል ይሰጣል። ከሌላ አካባቢ ወደ ማዕከሉ መምጣት የሚፈልጉ ተማሪዎችንም ይቀበላል። ማዕከሉ ሁሉም ተማሪዎች የተቀመጠውን መመዘኛ መስፈርት እስካለፉ ድረስ የሚቀበላቸው ሲሆን፣ በአቂቃ ቃሊቲ ዙሪያ ብቻ የትራንስፖርት /ሰርቪስ/ አገልግሎት በነጻ ይሰጣል፤ የትራንስፓርት አቅርቦት አለመኖር ለሌሎች አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ከሌላ ቦታ ወደ ማዕከሉ ለመግባት ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ሌላ አማራጭ ተቀምጦላቸዋል። የትራንስፖርት አገልግሎት ባሉበት ቦታ መስጠት ባይችልም ተማሪዎቹ ማዕከሉ የትራንስፖርት አገልግሎቶችን በሚሰጥባቸው አቂቃ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የተለያዩ አካባቢዎች መምጣት ከቻሉ የትራንስፖርት አገልግሎቱን ማግኘት ይችላሉ።

ማዕከሉ አሁን በአንድ ዙር እስከ 300 ተማሪዎች እያሰለጠነ ይገኛል። ስልጠናው ዓመቱን በሙሉ ይሰጣል። የስልጠና መርሃ ግብሩ በጋ ቅዳሜና እሁድ፣ ክረምት መደበኛ ተማሪዎች ስለማይኖሩ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ በሥራ ሰዓት ይሰጣል። በየሁለት ወሩ ሦስት መቶ ተማሪዎችን አሰልጠኖ ያስመርቃል።

በቱርክ ለሚካሄደው ሮቦቲክ ኦሎምፒያድ በየማዕከላቱ በሮቦቲክ የሰለጠኑ ሁሉም ሰልጣኞች በሮቦቲስ የሰሩትን እንዲያቀርቡ መደረጉን ያስታወሰው አቶ አለም ሰገድ፤ 27 የማዕከሉ ተማሪዎች የሮቦቲክ ስልጠና ከወሰዱ በኋላ ሦስት ሦስት ሆነው በቡድን ፕሮጀክቶችን እንዲሰሩ መደረጉን ይገልጻል። ከእነዚህ መካከል የተመረጡ አራት ፕሮጀክቶች መቅረባቸውን አስታውቆ፣ አስራ ሁለት ተማሪዎች በየፕሮጀክቱ ሦስት ሦስት ተማሪዎች የሰሩት ፕሮጀክት ለውድድር አቅርበዋል ብሏል። እነዚህ አስራ ሁለት ተማሪዎች በተለያየ መመዘኛ መስፈርት መሰረት ተወዳደረው ስለተመረጡ ፕሮጀክቶቹ በዓለም አቀፍ ውድድር ላይ እንዲቀርቡ መደረጉን አብራርቷል።

አስተባባሪው እንደሚለው፤ ስቲም ፓወር ኢትዮጵያ የተለያዩ ፕሮጀክቶቹ ግብዓት የሚሆኑ የቁሳቁስ ድጋፍ ለማዕከሉ አድርጓል። የተቀሩት ለፕሮጀክቱ አስፈላጊ ግብዓቶች በዩኒቨርሲቲው ተሟልተው ሥራዎች ተሰርተዋል። በተለይ ወደ ማዕከሉ መጥተው ስልጠናውን ከወሰዱ 12 ተማሪዎች መካካል በፆታ አንጻር ሲታይ 7ቱ ሴቶች ሲሆኑ፣ የተቀሩት አምስቱ ወንዶች ናቸው። እነዚህ ተማሪዎች ናቸው አራት ፕሮጀክቶች ሰርተው ለውድድሩ ያቀረቡት።

ለዓለም አቀፉ ውድድር የቀረቡት አራት ፕሮጀክቶች ሁሉም ሮቦቶች ናቸው። ፕሮጀክቶቹ አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ወይም ከተፈጥሮ ጋር ተሰማምተው አካባቢ ላይ ምንም አይነት አሉታዊ ተፅእኖ ሳይፈጥሩ የሚሰሩ ሮቦቶች የተሰሩባቸው ናቸው። አንደኛው ፕሮጀክት የሃይድሮ ፎኒክ ሲስተም/ ለግብርና ሥራ የሚውል/ ፋርሚንግ ሲስተም/ ነው። ይህም አፈር ሳያስፈልግ ለአትክልቶቹ የሚያስፈልጉትን ንጥረ ነገሮች ብቻ አትክልቶቹ ወደ ተተከሉበት ፕላስቲክ የሚያስገባና መጠነ ሙቀት፣ በውሃ ውስጥ ያለውን የጨው መጠን፣ የአሲድ ወይም የቤዝ መብዛት እና አለመብዛቱን እየለካ የሚያመጣጥን ሮቦት ነው።

ሁለተኛው ፕሮጀክት ለአሣ እርባታ የሚያገለግል ሮቦት ነው። ሮቦቱ በኩሬ ውስጥ በተሞላው ውሃ አሞኒያ የተሰኘው ንጥረ ነገር መኖሩን አረጋግጦ ካለ እንዲወጣ ያደርጋል። አሞኒያ አሳዎችን ስለሚገድል በሮቦቱ ሴንሰር አማካኝነት የአሞኒያ ጋዙ ከውሃ ውስጥ እንዲወጣ ያደርጋል። በተለያየ ምክንያት ሊመጣ የሚችለውን ጨው መኖር አለመኖሩን እንዲሁም በምን ያህል መጠን እንዳለ በማረጋገጥ እንዲወገድ ያደርጋል።

የአሲድም(ቤዝ) ጥንካሬ እየጨመረ ሲመጣ አሳዎችን ይገድላል ወይም ለእድገታቸው ምቹ ያልሆነ ሁኔታ እንዲፈጠር ምክንያት ሊሆን ይችላል ያሉት አቶ አለምሰገድ፣ ይህንን እያረጋገጠ ውሃው ንጹህ እንዲሆን ያደርጋል። ሌላኛው አሳዎቹን በሰዓት እየጠበቀ ይመግባቸዋል። ያለምንም እጋዥ ራሱን በራሱ መቆጣጠር የሚችል ሮቦት ነው።

ሦስተኛው ፕሮጀክት ሆስፒታል ውስጥ ለታካሚዎች ሰዓት ጠብቆ ምግባቸውን እንዲወስዱ ትዕዛዝ የሚሰጥ ሮቦት ነው። አራተኛውና የመጨረሻው ሮቦት ዓይነሥውራን የሚያግዘው ነው። የብሬል ፊደሎች በሁሉም ቤት የለም ያለው አቶ አለምሰገድ፣ ተማሪዎች ብሬል ሊያገኙ የሚችሉት ትምህርት ቤት ብቻ ነው፤ አንደኛ ደረጃ ላይ ያሉ ተማሪዎች ይህን ለማግኘት ረዳት ወይም አጋዥ ይፈልጋሉ፤ ይህንን ድጋፍ የሚሰጥ ሮቦት ነው የተሰራው። ፊደሉን ሲነኩ፣ ምን ፊደል እንደሆነ የሚነግር ሮቦት ነው።

ማዕከሉ እነዚህን አራት ፕሮጀክቶች ለዓለም አቀፉ የሮቦቲክ ኦሎምፒያድ ውድድር ይዞ የቀረበ ሲሆን፤ ከአራቱ ፕሮጀክቶች አንደኛው አሣ እርባታ ላይ የሚያገለግለው ሮቦት ሦስተኛ ደረጃ በመውጣት አሸናፊ ሆኖ ተሸልሟል።

## ወቅታዊ ትንታኔ

# ገበያ መሩ የውጭ ምንዛሪ ጅማሮ

**ምሕረት ሞገስ**

በሐምሌ 22 ቀን 2016 ዓ.ም የውጭ ምንዛሪው በገበያ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን በሚል ትልቅ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ለውጥ መደረጉ ይታወሳል። ሶስት ወራትን ለማስቆጠር ሶስት ቀን የቀረው ይህ «ፍሎቲንግ» ገበያ መር የውጭ ምንዛሪ ሥርዓት ርምጃ ምን ውጤት አስገኘ? በርግጥስ ብዙ የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት፤ ጥቁር ገበያን ለማስቀረት አስችሏል? ጥቅም እና ጉዳቱስ ምን ይመስላል? ብለን ላቀረብናቸው ጥያቄዎች የዘርፉ ምሁራን የሚሉት አላቸው።




በኢትዮጵያ ኢኮኖሚክ አሶሴሽን በተመራማሪነት በማገልገል ላይ የሚገኙት ሞላ ዓለማየሁ (ዶ/ር) እንደሚያስረዱት፤ የውጭ ምንዛሪ ገበያ መር ይደረግ ሲባል መነሻው ገበያው ይወስነው ከሚል ነው። ይህ ማለት አንዳንድ በሀገራችን ላይ ተቀባይነት ያላቸው የውጭ ገንዘቦች የሽያጭ ሁኔታቸው ባላቸው የአቅርቦት መጠን ላይ ይወሰን ለማለት ነው። እዚህ ላይ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት እጅግ ውስን ይሆናል። የውጭ ምንዛሪ ግብይት ላይ ነገሮችን ፈር ከማስያዝ የዘለለ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት አይኖርም ማለት ነው።

የውጭ ምንዛሪ ተመኑን የሚወስነው ገበያው ነው ሲባል፤ ምን ለማለት ነው ጥቅሙስ ምን ያህል ነው በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ ሞላ ዓለማየሁ (ዶ/ር) እንዳብራሩት፤ ጥቅሙን ለማብራራት በቅድሚያ የሀገሪቱን የገበያ ሁኔታ ማወቅ ወሳኝነት አለው። በተለይ ከአምራች ኢንደስትሪው ጋር ተያይዞ ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶች ብዙ ሆነው የውጭ ምንዛሪ ማስገባት ከቻሉ ሀገር ተጠቃሚ ትሆናለች። ምክንያቱም ዕቃዎችም ሆኑ አገልግሎቶች የተሻለ ገቢ የሚያስገኙ ይሆናል። እንደ ኢትዮጵያ አይነት ሀገሮች ላይ ግን ገበያ መር ማድረጉ የተወሰነ ጫና እንዳለው መካድ አይቻልም።

የገቢ ንግዱ ከውጭ ንግዱ በሶስት ነጥብ አምስት እጥፍ የበለጠ ሆኖ፤ ገበያ መር የምንዛሪ ሥርዓትን መጠቀም ምንዛሪው ገበያ መር መሆኑን ተከትሎ ዕቃዎች ውድ እንዲሆኑ ያስገድዳል። አሁን ባለው የግሽበት መጠን ላይ እንደገና የውጭ ምንዛሪን ገበያ መር ማድረጉ ሌላ የራሱን አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል። ስለዚህ ሊመጣ የሚችለውን ጫና ከመቀነስ አኳያ የመንግሥት ሚና ከፍተኛ ሊሆን ይገባል የሚል እምነት እንዳላቸው ያመለክታሉ።

ገበያ መር መሆኑ ሀገርም ሆነ ሕዝብን በርግጥ ምን ያህል እየጠቀመ ነው ? ጉዳቱ አያመዝንም ? በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ ሞላ ዓለማየሁ (ዶ/ር) በሰጡት መልስም፤ ከታወጀ አልቆየም። ገና የመዘጋጃ ጊዜ ላይ በመሆኑ አሁን ጥቅሙንም ሆነ ጉዳቱን ለማረጋገጥ ጊዜው አይደለም። በተጨማሪ በደፈናው ጠቅሟል ወይም ጎድቷል ከማለት ይልቅ ምላሽ ለመስጠት ጥናት ያስፈልጋል ብለዋል። አያይዘውም ነገር ግን አሁንም ቢሆን ገበያ መር ቢሆንም መንግሥት የተሻለ ሚና መጫወት አለበት ለዚህም ከመጠባበቂያው ላይ ቀንሶ የውጭ ምንዛሪውን ወደ ገበያው ማውጣት እንደሚጠበቅበት ጠቁመዋል።

ከአዋጁ በኋላ ባንኮች በተሻለ ዋጋ ለመግዛት እንቅስቃሴ እያደረጉ መሆኑን ጠቅሰው፤ እንደ አንድ ኢኮኖሚስት በእርሳቸው በኩልም ጥያቄ መኖሩን በመጠቆም ባንኮች ውድድራቸው በመግዛት ላይ እንጂ በማቅረብም ሆነ በመሸጥ ላይ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ አይታይም። ይህ ደግሞ በኢኮኖሚው ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ስላለው መንግሥት በዚህ ጉዳይ ዙሪያም አተኩሮ መሥራት እንዳለበት አመላክተዋል።

ሞላ ዓለማየሁ (ዶ/ር)፤ ጨምረውም ባንኮች የተሻለ የውጭ ምንዛሪ እያገኙ እንደሆነ እየተናገሩ ነው። ነገር ግን በበቂ መጠን ካላገኙ እጥረቱ እስካልተቀረፈ ድረስ ተፅዕኖ መኖሩ አይቀርም። ተፅዕኖውን ለማቃለል መንግሥት በድጎማ ወይም በተለያዩ መንገዶች እጥረቱን መቀነስ አለበት ሲሉ መክረዋል።

የውጭ ምንዛሪ የጥቁር ገበያ አሁንም እየታየ መሆኑን እና ይህ እንዴት ሊሆን እንደቻለ እንዲሁም ጉዳዩ የሚቀርበትን ሁኔታ በተመለከተ ለቀረበላቸውም ጥያቄ፤ ሞላ ዓለማየሁ (ዶ/ር) በሰጡት ምላሽ፤ ጥቁር ገበያ በተዘዋዋሪ ጉዳት ይኖረው ይሆናል። ነገር ግን መንግሥት በቢሮክራሲ ጥቁር ገበያን ለመቆጣጠር ጥረት ከሚያደርግ ይልቅ በሌላ በኩል ሌሎች ሥራዎችን ቢሠራ ይሻላል ብለዋል።

ዋናው ጉዳይ የውጭ ምንዛሪ ገበያ መር ተብሎ ከታወጀ ወዲህ በጥቁር ገበያው እና በባንክ ምንዛሪው መካከል ያለው ልዩነት ሲሆን ይህም በጣም ተቀራርቧል። ባለፉት ሁለት እና ሶስት ቀናት ውስጥ ጥቁር ገበያው ትንሽ በለጥ ያለ ቢሆንም፤ አሁንም እንደ በፊቱ ከመራራቅ ይልቅ እጅግ የተቀራረበ ነው። ይህ ደግሞ ጊዜያዊ የፍላጎት ጭማሪ በመሆኑ፤ የጥቁር ገበያው በጣም እየናረ ነው ለማለት የሚስደፍር አለመሆኑንም አመልክተዋል።

በየትኛውም መስክ የገበያ ውጣ ውረድ ይኖራል። ፍላጎት ሲጨምር ዋጋ ይጨምራል፤ ፍላጎት ሲቀንስ ደግሞ ዋጋ ይቀንሳል። በማለት የተናገሩት ሞላ ዓለማየሁ (ዶ/ር) ቢያንስ ለተወሰኑ ወራቶች ከታየ በኋላ የጥቁር ገበያው መልክ ይይዛል ብለዋል። ዋናው መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ አቅርቦት እና ፍላጎት እስካልተጣጣመ ድረስ ጥቁር ገበያው መኖሩ አይቀርም። ነገር ግን በሁለቱ መካከል ያለው ክፍተት እየጠበበ መምጣቱ የሚካድ አይደለም። ይሄ ደግሞ ዋነኛ የጥቁር ገበያውን የመከላከያ መንገድ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

የሲዳማ ባንክ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ታደሰ ሐጢያ በበኩላቸው፤ አዋጁን ተከትሎ መንግሥት የውጭ ምንዛሪን ፈሰስ አድርጓል። የውጭ ምንዛሪው ገበያ መር ሲሆን፤ የተለያዩ ባንኮች እንዲገዙ ለማገዝ የተለቀቀ ገንዘብ ባንኮችን ደግፏል። በተጨማሪ ከውጭ ሀገር የሚላከውም ገንዘብ ስለጨመረ ባንኮች የውጭ ምንዛሪ እያገኙ ነው። ያገኙትን የውጭ ምንዛሪ ደግሞ እየሸጡ ነው። በባንክ በኩል የውጭ ምንዛሪውን ይዞ መቆየት አክሳሪ ነው። ምክንያቱም ባንኩ ራሱ ትርፍ የሚያገኘው ደንበኞች ባለው ገንዘብ ሲጠቀሙ በመሆኑ ነው።

የሀገር ውስጥ ገንዘብም ቢሆን ተመሳሳይ ነው። በቢሊየን ቁጥር የገባ ብር መንቀሳቀስ አለበት። አዲሱ ፖሊሲ ብዙ የውጭ ምንዛሪ እንዲገባ አድርጓል። በተመሳሳይ መልኩ ለደንበኞች የውጭ ምንዛሬ ለማቅረብም ጥሩ ዕድል ፈጥሯል። ያሉት አቶ ታደሰ በእነርሱ በኩል ያገኙትን የውጭ ምንዛሪ እየሰጡ መሆናቸውን እና የሚደብቁበት ሁኔታ አለመኖሩንም ይናገራሉ።

ኢኮኖሚስቱ ብርሃኑ ደኑ ( ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ ገበያ መር በሆነ ኢኮኖሚ ውስጥ ብዙ ነገሮች መንግሥት ከላይ ሆኖ ወደ ታች የሚያስተላልፈው ሳይሆን በፍላጎት እና በአቅርቦት ላይ ተመስርቶ የሚወሰን ነው። ዕቃውም ሆነ አገልግሎቱ የሚሸጠው እና የሚገዛው በዚሁ በአቅርቦት እና በፍላጎት ላይ ተመስርቶ ነው። የገንዘብ ሽያጭም ተመሳሳይ ነው። ይህ ሳይንሳዊ የኢኮኖሚ እውነት ነው። ነገር ግን ሲተገበር የኢኮኖሚዎቹ አቋም በምን ዓይነት የልማት ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ታሳቢ ማድረግ ደግሞ ያስፈልጋል።

በሌላ በኩል በአሁኑ ጊዜ በግሎባላይዜሽን ዘመን አንድ ሀገር ለብቻዋ ተነጥላ መኖር አትችልም። የዓለም ሀገሮች በአብዛኛው በንግድ፣ በኢኮኖሚ፣ በኢንቨስትመንትም ሆነ በፖለቲካ ፣ በማህበራዊ ሁኔታም እየተገናኙ የሚኖሩ ናቸው። ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ በአሁኑ ጊዜ ከዓለም ሁኔታ አንፃር የውጭ ምንዛሪ መንግሥት እንደ በፊቱ በብሔራዊ ባንክ በየጊዜው የሚወስነው የምንዛሪ ተመን ከገበያው ጋር መሔድ አልቻለም። በተጨማሪ በቂ የውጭ ገንዘብ አቅርቦት ማግኘት ስላልተቻለ የጥቁር ገበያው ዋጋ የመንግሥት ባንኮች ከሚመዘግቡት በጣም በከፍተኛ ዋጋ የጨመረ ነበር። አቅርቦቱ ከፍላጎቱ ጋር ስላልተመጣጠነ ሰው ሌላ አማራጭ ለመፈለግ ሄዶ ከፍተኛ የምንዛሪ ተመን በመስጠት ሲገዛ ቆይቷል ይላሉ።

እንደ ብርሃኑ (ዶ/ር) ገለፃ፤ ስለዚህ በመንግሥት ትዕዛዝ በብሔራዊ ባንክ ተመን መሠረት በየጊዜው ለባንኮች እየተነገረ የሚሰጠው ዝቅተኛ የባንኮች ተመን ዋጋ ቢኖርም፤ የውጭ ምንዛሪ የሚፈልግ ሰው ከዛ በላይ ለመክፈል ፍላጎት እንዳለው አመልካች ነገሮች ነበሩ። በግልፅ በአደባባይ እንደታወቀው፤ መንግሥት ሃምሳ ብር አካባቢ እየመነዘረ ጥቁር ገበያው መቶ ደርሶ ነበር። ያ ደግሞ በዛ ዋጋ ለመግዛት የሚሻ ፍላጎት አለ ማለት ነው። ስለዚህ በርዳታም ሆነ በዕዳ ሽግሽግ ከውጭ ካሉ የልማት ድርጅቶች አጋዥነት የአቅርቦቱን መጠን ከፍ ለማድረግ ተሞክሯል።

በተጨማሪ በተለያየ ሁኔታ በሙስናም ቢሆን ጥቁር ገበያም ባይኬድ አንድ ዓይነት የምንዛሪ ተመን እንዲሆን የገበያው ሁኔታ ለቀቅ ይደረግ፤ ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው ጣልቃ እየገባ ይህን አድርግ ብሎ ከሚያዝ በየጊዜው የሚቀያየር ሳይሆን በገበያው ላይ ለማንም በማያደላ ተወዳዳሪነት ባለው ሁኔታ ምንዛሪው ይዳኝ ተብሎ ተወሰነ። ስለዚህ ካለው ከጥቁር ገበያ ጋር የሚስተካከልበት ሁኔታ እንዲፈጠር ተደረገ። አቅርቦቱ እየበዛ ሲሄድ ሰዎች በሚፈልጉት መጠንና ዋጋ በባንክ ማግኘት ከተቻሉ ወደ ጥቁር ገበያ አይኑን የሚያማትር አይኖርም በሚል ነው ይላሉ።

ይሄ መልካም ቢሆንም ከባንኮች ጋር ሕጋዊ ባልሆነ መልኩ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ካሉ አሁንም ገበያውን ይረብሻሉ። ይህ የታወቀ ነው። ሕገ ወጥ ንግድ እና የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ለማካሔድ የሚፈልጉ ካሉ፤ አሁንም መረበሻቸው አይቀርም። ባንክ የሚሔዱ ከሆነ በሕጋዊ መንገድ መሆን አለበት። ትክክለኛ እና አስተማማኝ ማስረጃዎችን በማቅረብ ማስፈቀድ ይገባል። በብድር እና በርዳታ የመጣውን የውጭ ምንዛሪ እንደፈለጉት ከሕግ ውጭ ማከፋፈል አይችሉም። ይህም ሆኖ ህጋዊ ሰነድ እና እውቅና የሌላቸው ይህንን ያጡ ሰዎች ወደ ጥቁር ገበያ መሄዳቸው አይቀርም።

ጥቁር ገበያውን ደግሞ በቀላሉ ዝም ብሎ ማሰር አይቻልም። አሁን አማራጭ ተወስዷል። አማራጩን የሚጠቀሙ አሁንም ቢሆን ከጥቁር ገበያው በተሻለ ሁኔታ በጣም ሕጉን በጠበቀ እና አስተማማኝ በሆነ መልኩ ያገኛሉ። ምክንያቱም አሁን በቀረበው ሪፖርት ባንኮች ባለፉት ወራት ከ282 ሚሊየን ዶላር በላይ ለተጠቃሚዎች አቅርበው፤ ከዚህ ውስጥ ግን እስከ አሁን ድረስ የተወሰደው 28 በመቶ ብቻ መሆኑ ይፋ ተደርጓል። ከባንኮች የመውሰድ ፍላጎት ለምን ቀነሰ ? የሚለው ሲታይ ድሮ በሕጋዊ መንገድም ሄደው ስለሚቆይባቸው እና ስለሚንገላቱ ስለሚያጡ ከጥቁር ገበያ ይገዙ ነበር። አሁንም ሕጋዊ በሆነ መንገድ ተመዝግበው የንግድ ፍቃድ ያላቸው ገንዘቡን እየተጠቀሙ መሆኑን ያስረዳሉ።

እንደ ብርሃኑ (ዶ/ር) ገለፃ፤ ነገር ግን አሁንም ቢሆን በተለያየ ሁኔታ ለተለያየ እንቅስቃሴ ሕጋዊ ሰነድ የሌላቸው የሚንቀሳቀሱት በጥቁር ገበያው ነው ማለት ነው። ስለዚህ ይህ ሁሉ በመሆኑ አንዳንድ ነገሮች በአጭር ጊዜ ውስጥ ላይስተካከሉ ይችላሉ። የትኛውም ለውጥ ጊዜ ይወስዳል። ጊዜ ይፈልጋል። ዛሬ የተደረጉ ማሻሻያዎች ቢያንስ ከስድስት ወር እስከ አንድ ዓመት ውጤታቸው ላይታይ ይችላል። ስለዚህ ጥቁር ገበያው የቀጠለው በሕገወጦች ምክንያት ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ያ እየተስተካከለ ሲሔድ፤ ሕገ ወጥ አካሔድን የሚከተሉ ሰዎች በሩ እየተዘጋባቸው ሲሔድ፤ ፍላጎታቸው ይቀንሳል። በዚህ ጊዜ ሕጋዊው የባንክ የገንዘብ ልውውጥ መንገድ ፈር እየያዘ ይሄዳል ብለዋል። በሌላ በኩል አንዳንድ የውጭ ምንዛሪው ገበያ መር እንዳይሆን የራሳቸው ፍላጎት ያላቸው ሰዎችም ይኖራሉ። ይህ ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ሳይሆን የትም ሀገር ሊሆን የሚችል መሆኑን አመልክተዋል።

እንደ ኢኮኖሚስቶቹ ገለፃ፤ ሳይንሱ ሲታይ የውጭ ምንዛሪ ተመኑን ገበያ መር ማድረጉ ጠቃሚ እና ተገቢ ነው። ነገር ግን ውጤቱን ወዲያውኑ ለማየት መጓጓት ትክክል አይደለም። በሂደት ለውጥ መገኘቱ አይቀርም። ሂደቱ ፈር እየያዘ ሲቀጥል የጥቁር ገበያ የሚቆምበት ሁኔታ እንደሚኖር አያጠራጥርም።

ማህበራዊ

# ሴቶች

## ባለነገዋ ማዕከል ተስፋን የሰነቀው የወጣቷ ሕይወት

**አመለወርቅ ከበደ**

አንድ ልጅ በሥነ ልቦናም ሆነ በአካል ጠንካራ ሆኖ እንዲያድግ እና ለስኬት እንዲደርስ የተረጋጋ ቤተሰብ አይተኬ ሚና አለው። የዛሬዋ ባለታሪካችንም በተረጋጋ ቤተሰብ ውስጥ የልጅነት ዘመኗን ማሳለፍ ባለመቻሏ በጎዳና ሕይወት ለአስከፊ ችግሮች ለመጋለጥ ተዳርጋ የነበረች ናት።

ዝናሽ በዛብህ ትባላለች፤ ወላጅ አባቷን አታውቀውም። እናቷ ሌላ ባል ስለአገባች ከእንጀራ አባቷ ጋር መኖር የግድ ይሆንባታል፤ እንጀራ አባቷ ግን አልተመቻትም። የራሱን ልጆች እንድትጠብቅለት እንጂ እንደ እኩዮቿ ወጥታ ከትምህርት ገበታ በሚገባ እንድትቋደስ እድሉን አልሰጣትም። የተሻለ ቢሆን ብላ በማሰብ እናቷ ወደ ቤተሰቦቿ ብትወስዳትም፤ የእናቷ እናት አባት /አያቶቿም/ ሥራ ጫና ስለሚያሳድሩባት አሁንም ለመማር እድሉን አላገኘችም።

እናት አሁንም ግራ ሲገባት ዝናሽን ገና ለሥራ ባልደረጀ እድሜዋ፤ ሰርታ እንድትበላ ወደ አዲስ አበባ ከተማ ላከቻት፤ አዲስ አበባም ዝናሽን እንዳሰበችው በደስታ አልተቀበለቻትም። «ለነገዋ የሴቶች ማገገሚያ ማዕከልን እስክትቀላቀል ድረስ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች እያደረች፤ በሱስ አረንቋ ተዘፍቃ በመሞትና መኖር መሃል ሆና ለመኖር ተገደደች።

ዝናሽ ትውልዷ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በወላይታ ዞን ነው። ዝናሽና ቤተሰቦቿ ግን በሥራ ምክንያት «ዎይጦ» በሚባል አካባቢ ነበር የሚኖሩት። "ወላጅ አባቴ ማን እንደሆነ አላውቅም፤ ስመጣ ስንት ዓመቴ እንደሆነም አላውቅም። ከህጻንነቴ ጀምሮ ያደኩት በእንጀራ አባቴ ስር ሆኜ ነው። ትምህርት ብጀምርም፣ እኩዮቼ የደረሱበት ለመድረስ ግን እድሉን አላገኘሁም። ምክንያቱ ደግሞ እንጀራ አባቴ ነበር፤ ትምህርት ያቋረጥኩበትንም አጋጣሚ ዛሬም ድረስ አስታውሰዋለሁ።» ትላለች።

"አንድ ቀን ትምህርት ቤት ሄጄ ስመለስ ለምን ልጆቹን ጥለሽ ሄድሽ ብሎ እንጀራ አባቴ በጣም ደበደበኝ። ከዛ በኋላም ትምህርት ቤት መሄድ ብጀምርም፣ ሁልጊዜ ከትምህርት ቤት ስመለስ የእንጀራ አባቴ ይሄን አጠፋሽ፣ ይሄን አደረግሽ ብሎ ይቆጣኝና ይመታኝ ስለነበር ትምህርቴን መቀጠል የምችልበት ሁኔታ አልነበረም። በዛ የተነሳ በልጅነቴ መማር እየፈለኩ ሳልማር ቀረሁ። " ስትልም ታብራራለች።

እንጀራ አባቴ እንድማር ሳይሆን፤ ልጆቹን እንድንከባከብለት ብቻ ነው የሚፈልገው። አያቴ አጠገብ ስቀመጥ ደግሞ የሥራ ጫና ይበዛብኛል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለሁ በአንድ ወቅት እናቴ ለበዓል ወደ ቤተሰቦቿ «አረካ» ወደ ምትባል ከተማ ይዛኝ ሄደች። በዛ ወቅት እናቴ እኔን የት ማስቀመጥ እንዳለባት በጣም ግራ ገብቷት ነበር። በመጨረሻም አማራጭ ስታጣ ሰርቼ እንድበላ በሚል ወደ አዲስ አበባ ላከችኝ ትላለች።

ዝናሽ በወቅቱ ወደ አዲስ አበባ ስትመጣ ብቻዬን ነኝ ብላ አልፈራችም። ምክንያቱም ከነበረችበት ሁኔታ አኳያ ስትመለከተው የተሻለ ነገር አገኛለሁ የሚል ሙሉ ተስፋ ነበራት። በደላላ አማካኝነት ለቤት ሠራተኝነት ተቀጠረች፤ ነገር ግን የሰው ቤት የኑሮ ጫናን መቋቋም አልቻለችም።

በተቀጠርኩበት ቤት እንድሰራ የምታዘዘው ነገር በሙሉ ከአቅሚ በላይ እየሆነ መጣ። ‹‹በወቅቱ እኔ ገና ልጅ ስለነበርኩ እና አቅሜም የጠነከረ ባለመሆኑ ብዙ ጉልበት የሚጠይቁ ሥራዎችን ለረዥም ሰዓት መሥራት እያቃተኝ መጣ። በየቀኑ አንድ ትልቅ ቤት እና አራት የልጆች ክፍሎችን ብቻዬን ማጽዳት ይጠበቅብኝ ነበር። ይህንን ስጨርስ ደግሞ በየእለቱ ሌሎች የምታዘዛቸው በርካታ ሥራዎች አሉ›› ስትል የደረሰባትን ጫና ታብራራለች።

ዝናሽ ወደ እንደዚህ አይነት የሚያደክም ሥራ ሰርታ አታውቅም ፤ በዚህ ላይ ምግብ በሥርዓቱ አይሰጣትም። ‹‹ቁርስ እንድበላ የሚፈቀድልኝ አምስት ሰዓት ላይ ነው፤ የሚሰጠኝም አንድ ዳቦና ሻይ ብቻ ነው። በዚህ አይነት ተቀጥሬ በምሰራበት ቤት የኑሮ ጫናው በጣም ሲከብደኝና ከአቅሜ በላይ እየሆነ ሲመጣ ተማረርኩና የሰራሁበትንም ገንዘብ ሳልቀበል ልብሴንም ሳልወስድ ከቤት ጠፍቼ ወጣው›› ስትል ገልጻለች። ዝናሽ ከዚያ በኋላ ተመልሳ ሰው ቤት አልተቀጠረችም። የምትሄድበት ዘመድም አልነበራትም፤ የጎዳና ሕይወትን ተቀላቀለች።

ዝናሽ በተቀጠረችበት ቤት በየእለቱ ይገጥማት የነበረውን ችግር አልፋለሁ ብላ የደረሰችበት ውሳኔ እንደሰባቸው ሳይሆን ሌላ ጉድ አስከትሎባት አረፈው። ምንም ለውጥ፣ ምንም ሰላምና እረፍት ሳታገኝ ወደ አዲስ አበባ መጥታ መኖር ከጀመረች ዓመታት ተቆጠሩ። በእነዚህ ዓመታት እናቷን ተመልሳ ሄዳ ለመጠየቅም አልቻለችም ። ምክንያቷ ደግሞ እናቷ የምታውቀው ሰው ቤት ተቀጥራ እየሰራች እንደሆነ ነው። የዝናሽ የእለት ከእለት ጥያቄ ከጎዳና ሕይወት እንዴት ልውጣ ? ወደ እናቴ እንዴት ልሂድ ? የሚል ሆነ።

ከገባችበት አጣብቂኝ በቀላሉ መፋታት አቃታት። አንዴ ጎዳና ላይ የወጣ ሰው በማህበረሰቡ የሚሰጠው ግምት አሉታዊ መሆኑ ይበልጥ እያመማት መጣ፤ በዚህ ሕይወት ውስጥ የቆየ ሰው ዋስ አያገኝም፤ እናም ሰው ቤት ተቀጥሮ መሥራትም ሆነ በሆቴልና በመሳሰሉት አስተናጋጅነትን ማግኘት የማይታሰብ ሆነ።

አንድ የነበራት አማራጭ ሃሳብ በተለምዶ «ጀብሎ» የሚባለውን ሥራ ነው። ይህም በየጎዳናው እየዞሩ እንደ ሲጋራ፣ ሶፍት፣ ማሲቲካና የመሳሰሉትን ቀላል ሸቀጦች በካርቶን እያዞሩ መሸጥ ነበር። ዝናሽም በዚህ እንኳን ብለወጥ ብላ በቀጥታ ወደ ሥራው ገባች።

ሥራውን የጀመረችው የ40 ብር ሶፍት ገዝታ በመሸጥ ሲሆን፣ ከዛ በኋላ ማስቲካና ሌሎች ነገሮችንም በመጨመር አስፋፋችው፤ ይሁንና እሱም ሳይሳካላት ቀረ። ‹‹አንዳንድ ሰዎች በኋላ እከፍላለሁ ብለው ሲጋራ ይወስዱና ገንዘቡን አይሰጡም፡›› ትላለች።

በመሀል ሌላ ነገር አስባ ሲጋራ መሸጡን አቆመችው። ‹‹እቃዎቼን ዘበኛ ቤት በክፍያ እንዲያስቀምጡልኝ ተስማማን። "እቃውን እንዲጠብቁ ያስቀመጥኩት ቦታ ተመልሼ ለመውሰድ ስጠይቅ ሁለት ሺህ ብር ተጠየኩ። እንዴት ለዚህ ትንሽ እቃ ሁለት ሺህ ብር እከፍላለሁ ብዬ ብከራከርም። እቃውን ካስቀመጥሽ ብዙ ጊዜ ስለሆነ የኪራዩ አድጓል አሉኝ›› ያለችው ዝናሽ፣ ይህን እቃም ሌላ ሥራ ሰርቼ የእቃውን ብር መልሼ አገኛለሁ ብላ ተወችላቸው።

ምንም እንኳን ዝናሽ በወቅቱ የተወረሰባትን እቃ ሰርታ እንደምትተካው አስባ የነበረ ቢሆንም ፣ ተመልሳ ወደ ሥራ ለመሰማራት ሳትችል ትቀራለች። ይልቁንም የተለያዩ ሱሶች ውስጥ በመግባት ጎዳና ላይ መዞር፣ የቀን ተቀን ተግባሯ ሆነ። የመሥራት እና የመለወጥ ህልሟም በሱስ ውስጥ ተደበቀ። ከጓደኞቿ ጋር በየሆቴሉ በመሄድ የምግብ ትራፊ ለምኖ መብላትና ጎዳና ላይ ሲዞሩ ውሎ እዛው ጎዳና ላይ ማደር ሕይወቷ ሆነ። አብዛኛው የጎዳና ተዳዳሪ እንደሚያደረገው ሁሉ ብርዱንም ለመከላከል ረሀቡንም ለመረሳት እንደ ማስቲሽ ያሉ የሚያደነዝዙ ነገሮችን መጠቀምም ትጀምራለች።

‹‹ማስቲሽ በጣም እጠቀም ነበር፤ ምክንያቱም እሱን ከወሰድኩ በረዶ የቀላቀለ ዝናብ እንኳን ቢጥል፣ ልብሴ ይበሰብስ ይሆናል እንጂ እኔ አይሰማኝም›› የምትለው ዝናሽ፣ እሱንም ማግኘት በጣም አስቸጋሪ እንደነበር ታስታውሳለች። ማስቲሹን የሚሸጡልን ሰዎች ከቦታው በትንሽ ብር ቢያመጡም ለእኛ ግን የሚሸጡት በ100 ብር ነበር። እኔ ደግሞ እንደ ጓደኞቼ አለምንም፤ የሱስ ጥያቄዎችን ለመመለስ ከጓደኞቼ እበደራለሁ ወይም እነሱ ይሰጡኛል። ለቁም ነገር ሲሆን እንጂ፣ ለሱስ ሲሆን ሰው ለመስጠት አይሰስትም›› ትላለች።

ለሱስ የሚሆን ገንዘብ ተበድራ ብትወስድም የመመለስ አቅሙ የሌላት ዝናሽ፣ "እኔ መለመንም



ዝናሽ በዛብህ

ስለማልችል ከየት አምጥቼ እመልሳለሁ፤ ገንዘቡን ከወሰድኩ በኋላ ተደብቄ ነው የምንቀሳቀሰው። ብዙ ጊዜ ቢያበድሩኝም መልሰው አይጠይቁኝም፤ እኔም ካገኘሁ ግን እከፍላለሁ" ትላለች። በዚህ አይነት አስፈሪና ተስፋ አስቆራጭ ሕይወት ውስጥ እያለች ነበር ሕይወቷን የሚቀይር አጋጣሚ የተፈጠረው። የነገዋ የሴቶች ማገገሚያ ማዕከልን እንድትቀላቀል ተደረገ።

ማዕከሉን የተቀላቀለችበትን አጋጣሚ ታውስታወሳለች። « ወደ ማዕከሉ ልገባ የቻልኩት እንዲህ ነው፤ አንድ ቀን ጠዋት ተኝታ ባለችበት ወደ ቤቷ የሄዱ ልጆች የነገዋ የሴቶች ማገገሚያ ማዕከል የሚባል ድርጅት እንዳለ ይነግሯታል፤ ሕይወትሽ እንዲስተካከል ለምን እዛ አትገቢም ብለው ይጠይቋታል።

እሷም ወደ ማዕከሉ የገቡ ጓደኞች እንዳሉ ታውቃለች። ከእነሱም ስለማዕከሉ የሰማችው ስለነበር ሳታመነታ ወደ ማዕከሉ እንደምትገባ አረጋጠችላቸው። መዘገቧት፤ ‹‹ወዲያውኑ ወደ ማዕከሉ እንደምሄድ ተነገረኝና ይዘውኝ ተንቀሳቀሱ። ለተወሰነ ጊዜም ዘነበ ወርቅ አካባቢ ማቆያ ውስጥ ከሰነበትኩ በኋላ ወደ ነገዋ ማዕከል ገባሁ›› ስትል እንዴት ወደ ማዕከሉ እንደገባች ገልጻለች።

ጎዳና ላይ እያለሁ ወደ እንደዚህ አይነት ማዕከል እመጣለሁ ብዬ አንድም ቀን አስቤ አላቅም። ወደ ማዕከሉ በምመጣበት ወቅትም እንደዚህ ሁሉም ነገር የተመቻቸለት ይሆናል ብዬ አላሰብኩም ያለችው ዝናሽ፣ ማዕከሉ ጉብታ ያለውን ነገር ስትመለከት ደስታዋን መግለጽ ተስኗት ነበር።

ሌሎች ድርጅቶች ሲረዱ ገንዘብ ብቻ የሚሰጡት። ይህ ማዕከል ግን ከፉና ደጉን እንድንለይ ጭምር አድርጎኛል ያለችው ዝናሽ፣ ጎዳና ላይ የነበረን ሕይወት በጣም አስከፊና አሳዛኝ ነበር፤ ከርሃቡ እና ከብርዱ ባሻገር በተባይ በጣም ተቸግሬያለሁ፤ የምቀይረው ልብስም አልነበረኝም። በየቀኑ ስለብሰው ከነበረው አንድ ቁምጣ፣ ቲሸርት እና አሮጌ ጃኬት ውጭ ሌላ ቅያሪ የሚባል ልብስም አልነበረኝም›› ስትልም አስታወሳለች።

"ጎዳና እያለሁ በንጽህና ጉድለት ምክንያት ፀጉሬ በተባይ የተሞላ ነበር፤ ስካርፍ አስሬ ነበር የምዞረው። መታጠብ ብዙም አይታሰብም፤ አንዳንድ መታጠቢያ ቤቶች ቢኖሩም፣ የሚያስከፍሉት 15 ብር ነው። ያን ብር ደግሞ ማግኘት ለእኔ ከባድ ነበር፤ ፀጉሬ እንዲህ ያደገውና የተዋበው ወደ ማዕከሉ ከገባሁ በኋላ ነው። » ትላለች።

በዚህ ላይ እናቷን ወደ ትውልድ አካባቢዋ ተመልሳ ሄጄ ለማየት በጣም ብትፈልግም ነገሮች የሚሳኩ አልነበሩም። ይህ ሁሉ ተደማምሮ አንዳንድ ጊዜ ምሬቱ ሲበዛበት ብቻዋን ታለቅስ እንደነበርም ትናገራለች።

ዝናሽ ጎዳና ላይ ያሳለፈችው ሕይወት እጅጉን አስከፊ ስለነበር የለመደችውን ተቆጣጣሪ የሌለበትን ኑሮ በመተው አዲስ ሕይወት ለመጀመር በውስጧ የፍርሃት ስሜት አላደረባትም። ወደ ማዕከሉ ለመግባት አንድ ስጋት ብቻ ነበረባት፤ እሱም በጎዳና ከለመደችው የማስቲሽ ሱስ እንዴት እላቀቃለሁ የሚለው ብቻ ነበር። እሱንም ቢሆን ከዛ አስከፊ ኑሮ ለመውጣት ወስና ስለነበር አምርራ ታገለችውናም ነገሮች ሁሉ ተሳኩላት።

ዝናሽ በአሁኑ ወቅት ከዚያ ሁሉ ስቃይ የበዛበት ሕይወት ተላቃ በማዕከሉ በነበራት ቆይታ የሆቴል መስተንግዶ ስልጠና ወስዳ ለመመረቅ በቅታለች። በስልጠናው ሆቴል ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ማሽኖችን እንዴት ማንቀሳቀስ እንደሚቻል፤ እንግዳን እንዴት ማስተናገድ እንዳለባት እና ሌሎች አስፈላጊ ትምህርቶችን ለመቅሰም በቅታለች።

በዘርፉ ስልጠና ለመውሰድ የፈለገችው በማንም ግፊት ሳይሆን በራሷ ፍላጎት እንደሆነም ትናገራለች። እነ ዝናሽ ወደ ማዕከሉ ገብተው አንድ ወር ከተቀመጡ በኋላ ነበር የሚሰለጥኑበትን የሙያ ዘርፍ እንዲመርጡ እድሉ ተሰጥቷቸው ነበር።

ሙያውን የመረጥኩት ራሴ ነኝ፤ በወሰድኩት ስልጠናም በጣም ደስተኛ ነኝ ስትልም ትገልጻለች። ዝናሽ በቀጣይ በሰለጠነችው ዘርፍ ለተወሰነ ጊዜ ከሰራች በኋላ እናቷን ሄዳ ለመጠየቅ እቅዳለች። ከዚያም ስትመለስ ሥራዋን ጠንክራ በመሥራት በተቻላት አቅም ሌሎች የተቸገሩ ሰዎችን ለመርዳት ሃሳቡ አላት። በማዕከሉ ላስተማሯት እና በአጠቃላይ ድጋፍ ላደረጉላት አካላት ሁሉ ምስጋናዋን አቅርባለች።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ግርማ መንግሥቴ**

በርካታ ፀሀፍት አዲስ ዘመን የዜጎችን ሁሉ ስሜት ሲያንፀባርቅ እንደኖረ ከትበዋል። የገበሬውም ሆነ ነጋዴው፤ የወንዱም ሆነ ሴቱ፤ የተማሪውም ሆነ አስተማሪው፤ በተለይም የጦር ሠራዊቱ ሁሉ ❖ ❖ ❖ አንደበት-ልሳን እንደ ነበር በህትመቶቹ ላይ በግልፅ ይታያል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፣ ለማሳያ ያህል በዚህ አምድ ላይ ለማስታወስ እየሞከርን እንዳለነው ጋዜጣው በተለያዩ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች ላይ ሳይታክት በብቸኝነት መረጃ ሲያቀብል ኖሯል። ዛሬም ከሀገር ፍቅር እስከ ❖ ❖ ❖ ድረስ ያሉ ሀሳቦች የተካተቱበት የትውስታ ዝግጅት እንደሚከተለው ቀርቧል።

### የዶላርን ነገር ጠንቀቅ

ኢንተርፖል የተባለው አለም አቀፍ የፖሊስ ድርጅት የዩናይትድ ስቴት የገንዘብ ሚኒስቴር የባንክ ኖቶቹን ባዲስ እንዲቀይር ምክር ለግሶታል። ለዚህ የተሰጠው አቢይ ምክንያት ከዩናይትድ ስቴት ጀምሮ በሁሉም የአለም ክፍሎች የውሸት ዶላሮች በዝውውር ላይ መገኘታቸው ነው። መረጃዎች እንደሚጠቁሙት እነዚህ የባንክ ኖቶች ስራ ላይ ከዋሉ ጀምሮ 12ሺህ የውሸት ዶላር "ሠዓሊያን" ወይም "አታሚ" ወንጀለኞች ለፍርድ ቀርበዋል። ይህ ቁጥር በዓለም ያሉትን የመስኩን ወንጀለኞች 90 በመቶ ያካተተ መሆኑን የፓሪስ ሌሞንድ ጋዜጣ ዘግቧል። እኛም የውጭ ንግዳችን በዚሁ የአሜሪካን ገንዘብ ስለሆነ ግርዱን ከፍሬው ለመለየት ጠንቀቅ ነዋ!

(አዲስ ዘመን፣ ጥቅምት 14 ቀን 1980 ዓ❖ም)

***

### በሬው ባለቤቱን ከጅብ አዳነው

(ከአዲስ ዘመን ጋዜጠኛ)

በጨርጨር አውራጃ ጭሮ ወረዳ ያብዶ ኮሎሎ በተባለው ቀበሌ በአቶ ወጋየሁ ወንድማገኘሁ መሬት ላይ እያረሰ የሚኖር አቶ ሙሳ ቡቲ የተባለ ገበሬ፤ሰኔ ፲፰ ቀን ፲፱፻፷ ዓ/ም ከሌሊቱ ፰ ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ በአንደኛው ቤት ውስጥ ካሉት ከብቶች መካከል አንዲት ፍየል ጅብ ጐትቶ ሲያወጣት ባለቤቱ ነቅቶ ጅቡን ሲከላከል ሆዱን ነከሰው፣ ሰውየውም የጅቡን አፍንጫውንና አገጩን አፍኖ ሲይዘው ሆዱን ለቆ የቀኝ ባቱን ነክሶ ፲፰ ሜትር ያህል ጐትቶ ሊበላው ሲተናነቅ የጥቁር ጋርማ ጐባ በሬ እውጭ ከታሠረበት ገመዱን በጥሶ ጅቡን ተከታትሎ በማባረር ባለቤቱን ከመበላት ያተረፈው መሆኑንና ሰውየውም በልዑል ሣህለ ሥላሴ ሆስፒታል ታክሞ የዳነ መሆኑን አቶ ወጋየሁ አስረድተውናል።

(አዲስ ዘመን ሐምሌ 7 ቀን 1960 ዓም)

*****

### ኢትዮጵያ በፀጥታ ምክር ቤት መቀመጫ እንዲሰጣት ጠየቀች

ከተባበሩት መንግሥታት ኢትዮጵያና ሞሪታንያ በፀጥታው ምክር ቤት ውስጥ አሁን በተባበረው ዓረብ ሪፑብሊክ የተያዘ የመካከለኛው መሥራቅ (ሥፍራ መቀመጫ) ለእኛ ይገባል ሲሉ ውድድር አቅርበዋል በማለት ከኒውየርክ የተገኘ ወሬ አስታውቋል።

ለምዕራበውያኑ አውሮፓ ክፍልና ለመካከለኛው ምሥራቅ እንዲሆኑ ጠቅላላ ስምምነት ተደርሶባቸው የነበረው መቀመጫዎች፤ሌሎችም የአፍሪካ አገሮች ለማግኘት በመከራከር ላይ እንደሚገኙ ተገልጿል።

ሌሎች መቀመጫውን ለመያዝ የሚወዳደሩ አገሮች ኢራን ሞሮኮና አፍጋኒስታን እንደሆኑ ታውቋል።

(አዲስ ዘመን ነሐሴ 24 ቀን 1954 ዓ.ም)

*****

### ይፍረድብኝ . . .

ምድርሽ ትፍረድ ❖ ❖ ❖ እፅዋትሽ፤
ለምለም ስፍራሽ ❖ ❖ ❖ ውብ አበባሽ፣
እናት አለም ጡት አጥብተሽ ❖ ❖ ❖ አሳድገሽ
ተንከባክበሽ ❖ ❖ ❖ ሁሉን አድርገሽ፣
ባለሽ አቅም ❖ ❖ ❖ አስተምረሽ፣
እናት ምድሬን ❖ ❖ ❖ እንዴት ልክዳሽ፣

እስኪ አዳምጮኝ እማምዬ

**አንቺ እናቴ**

ትቼሽ ብሄድ ❖ ❖ ❖ ኮብልዬ
ይለወጣል እኔነቴ?
እዚያም ብሄድ ❖ ❖ ❖ እዚያም ብደርስ፣
መልኬ ያው ነው አፍሪካዊ
የታወቅሁ ጥቁር ኢትዮጵያዊ
በቀውጢ ወቅት ❖ ❖ ❖ በችግርሽ
አንችን ትቼ ❖ ❖ ❖ አንችን ልሸሽ?
በብልፅግናሽ ❖ ❖ ❖ በሀብትሽ ወቅት
ስትላቀቂ ❖ ❖ ❖ ከረሀብ ❖ ❖ ❖ ከድህነት
ዙሬ ላይሽ ❖ ❖ ❖ ልመለስ?
ያፈራሽውን ❖ ❖ ❖ ፍሬ ልቀምስ?
ምድርሽ ይፍረድ ❖ ❖ ❖ የጎመራው
ወንዝሽ ይፍረድ ❖ ❖ ❖ የምጠጣው
ማሳደግሽን ❖ ❖ ❖ ማስተማርሽን
ይህን ዐቢይ ❖ ❖ ❖ ውለታሽን
በዜግነቴ ❖ ❖ ❖ ባለኝ አቅም
ውለታሽን ❖ ❖ ❖ አልመልስም?
የጠጣሁት የበላሁት ❖ ❖ ❖ ትዝ አይለኝም?
ወንዝ ጅረትሽ ❖ ❖ ❖ ይፍረድብኝ
ዳገት ቁልቁለቱ ❖ ❖ ❖ ዋጥ ያድርገኝ
የድንበር አጥርሽ ❖ ❖ ❖ አንቆ ይድፋኝ
ፍርዴን ላግኝ ❖ ❖ ❖ የሞት ቅጣት
ወገን ይያት ❖ ❖ ❖ የኔን ሕይወት
አንችን ብተው ❖ ❖ ❖ አንችን ብክድ
ብኮበልል ❖ ❖ ❖ ብጓዝ ብሄድ።

(ሀብቱ በላይ)

(አዲስ ዘመን፣ ታህሳስ 5 ቀን 1979 ዓም)

# ዓለም አቀፍ



## የደህንነት ስጋት ያለበት የእስራኤል ካቢኔ

ከአንድ ዓመት በፊት የፍልስጤሙ ሐማስ በእስራኤል ላይ ያልተጠበቀ ጥቃት መፈጸሙን ተከትሎ የተጀመረው ጦርነት አድማሱን እያሰፋ ይገኛል። ከአንድ ወር በፊት በሊባኖሱ ሂዝቦላህ እና እስራኤል ጦር መካከል ይፋዊ ጦርነት የተጀመረ ሲሆን የእስራኤል ጦር ወደ ደቡባዊ ሊባኖስ ገብቶ ከሂዝቦላህ ተዋጊዎች ጋር እየተዋጋ ይገኛል።

ሂዝቦላህ ወደ እስራኤል ከተሞች የአየር ላይ ጥቃቶችን በማድረስ ላይ ሲሆን፤ የጠቅላይ ሚኒስትር መኖሪያ ቤት፣ የሀገሪቱ የስለላ ተቋም ሞሳድ እና ሌሎች ወታደራዊ ተቋማት ዋነኛ ኢላማ ሆነዋል። ይህን ተከትሎ በጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታንያሁ የሚመራው የሀገሪቱ ካቢኔ መደበኛ ስብሰባ ቦታ ተቀይሯል ተብሏል። እንደ ዘ ታይምስ ኦፍ እስራኤል ዘገባ ከሆነ የሀገሪቱ ካቢኔ ስብሰባ ቦታ የተቀየረው በደህንነት ስጋት ምክንያት ነው።

ከዚህ በፊት የእስራኤል ካቢኔ ስብሰባ በሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ውስጥ ይደረግ የነበረ ሲሆን ከዛሬ ጀምሮ ግን በደህንነት ስጋት ምክንያት የስብሰባ ቦታው ተቀይሯል። ሂዝቦላህ በሰሜናዊ እስራኤል የ14 መኖሪያ መንደር ነዋሪዎች ቤታቸውን እንዲለቁ አስጠነቀቀ።

የካቢኔ ስብሰባው ከዛሬ ጀምሮ በአንድ ቦታ ሳይሆን በተለያዩ ቦታዎች ላይ ይካሄዳል የተባለ ሲሆን፤ ስብሰባው በቋሚ ቦታ እንዳይካሄድ ተወስኗል። ሂዝቦላህ በትናንትናው ዕለት በሁለቱ ድንበር አቅራቢያ ባሉ 14 መኖሪያ መንደሮች ውስጥ የሚኖሩ እስራኤላዊያን ቤታቸውን ባስቸኳይ እንዲለቁ ማስጠንቀቁ ይታወሳል።

ሂዝቦላህ በሰሜናዊ እስራኤል የሚኖሩ እስራኤላዊያን መኖሪያ ቤታቸውን እንዲለቁ ያስጠነቀቀው የሀገሪቱ ጦር ነዋሪዎች ባሉባቸው አካባቢዎች ሰፍሯል በሚል ነው። ነዋሪዎች ማስጠንቀቂያ ችላ ብለው ለሚደርስባቸው ጥቃት ኃላፊነቱን እንደማይወስድም ሂዝቦላህ አስታውቋል።

## ከአስር አሜሪካውያን አራቱ ከዘንድሮው ምርጫ በኋላ ግጭት ሊፈጠር እንደሚችል ያምናሉ ተባለ

አሜሪካ ወደ ቀድሞ የአመጻ ፖለቲካ እና ብጥብጥ ትመለስ ይሆን የሚለው ስጋት በርካታ አሜሪካውያን የሚጋሩት ሀሳብ ነው። አሜሪካውያን ከድህረ ምርጫ በኋላ ምን ሊከሰት ይችላል በሚል ጭንቀት ውስጥ ወደ 2024ቱ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ እየተቃረቡ ነው።

ይህ ጭንቀታቸው የድህረ ምርጫ ብጥብጥ እና ውጤቱን ለመቀልበስ የሚደረጉ ሙከራዎች የዴሞክራሲ ቁንጮ በተባለው የአሜሪካ ፖለቲካ ስርአት ላይ ተጽዕኖውን ሊያሳድር ይችላል ከሚል የመነጨ እንደሆነ ኤፒ ዘግቧል።

ከአራት አመት በፊት የ2020ውን ምርጫ ውጤት አልቀበልም ያሉት የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ፤ ደጋፊዎቻቸው ወደ ካፒቶል ሂል ሄደው ተቃውሟቸውን እንዲያሰሙ በይፋ ጥሪ ማድረጋቸው ይታወሳል።

ከዚህ ጊዜ በኋላ ደግሞ በዘንድሮው ምርጫ ቅስቀሳ ወቅት በሪፐብሊካኑ ዕጩ ትራምፕ ላይ ሁለት ጊዜ የግድያ ሙከራዎች እንደተቃጣባቸው አይዘነጋም። ይህንን ተከትሎም አሜሪካ ወደ ቀድሞ የአመጻ ፖለቲካ እና ብጥብጥ ትመለስ ይሆን የሚለው ስጋት በብዙ አሜሪካውያን መራጮች አዕምሮ ውስጥ የሚመላለስ ሀሳብ መሆኑ ተሰምቷል።

የአሶሼትድ ፕረስ የህዝብ ጉዳዮች የምርምር ማዕከል ባሰባሰበው የህዝብ ድምጽ ከአስር አሜሪካውያን መራጮች መካከል አራቱ ከዘንድሮው ምርጫ በኋላ ብጥብጥ እና የምርጫውን ውጤት ለመቀልበስ የሚደረጉ ጥረቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ስጋት እንዳላቸው ገልጿል።

በተመሳሳይ ከ3ቱ መራጮች መካከል አንዱ የአካባቢ ወይም የግዛት የምርጫ አስፈፃሚዎች ውጤቱ እንዳይጠናቀቅ ለማስቆም ፤ በምርጫው ጣልቃ ለመግባት ሙከራ ሊያደርጉ እንደሚችል እምነት አላቸው። ከዚህ ውስጥ ምርጫው በሰላም እንደሚጠናቀቅ እና ጤናማ የስልጣን ሽግግር ሂደት ሊኖር እንደሚችል እምነት ያላቸው አንድ ሶስተኛ ብቻ መራጮች ናቸው።




ከአራት አመት በፊት የተሸነፉት በተጭበረበረ ድምጽ እንደሆነ አሁንም መናገራቸውን የቀጠሉት ዶናልድ ትራምፕ፤ በዚህኛው ዙር ምርጫም ሊሸነፉ የሚችሉት በማጭበርበር ብቻ ሊሆን እንደሚችል መተንበያቸውን አላቆሙም።

የኤፒ የጥናት ማዕከል ባሰባሰበው ድምጽ በርካታ መራጮች ትራምፕ የሚሸነፉ ከሆነ ውጤቱን አምኖ ለመቀበል የሚቸገሩ እንደሚሆኑ ተናግረዋል። በዚህ ጉዳይ ዙሪያ በዴሞክራት እና ሪፐብሊካን መራጮች ዘንድ ያለው ሀሳብ የተለያየ ነው። ከሪፐብሊካን መራጮች መካከል ሁለት 3ኛ ያህሉ ትራምፕ ውጤቱን እንደሚቀበሉ ያስባሉ፤ በአንጻሩ ከ10 ዲሞክራቶች አንዱ ብቻ የምርጫውን ውጤት ሊቀበሉ እንደሚችል ተናግሯል።

ተቀናቃኛቸው ካማላ ሃሪስን በተመለከተ ከ10 ሰዎች መካከል ስምንቱ የምርጫ ውጤቱን በሰላማዊ መንገድ ሊቀበሉ እንደሚችሉ እምነት አላቸው። ነገር ግን በሁሉቱም መንገድ የዘንድሮው ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ የአሜሪካ የዴሞክራሲ ጉዞን የሚወስን ሊሆን እንደሚችል ከ50 በመቶ በላይ መራጮች ያስባሉ።

# ስፖርት





# ኢትዮጵያውያን አትሌቶች የደመቁበት የፍራንክፈርት ማራቶን

**ቦጋለ አበበ**




**ሀዊ ፈይሳ በአስደናቂ ብቃት የፍራንክፈርት ማራቶንን ክብረወሰን አሻሽላ አሸንፋለች፣**

የፍራንክፈርት ማራቶን ለ41ኛ ጊዜ ከትናንት በስቲያ ሲካሄድ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በጀርመኗ ከተማ ደምቀው ውለዋል። በሴቶች መካከል በተካሄደው ውድድር ሀዊ ፈይሳ የውድድሩን ክብረወሰን በማሻሻል ስታሸንፍ በወንዶች ከሁለት እስከ ስድስት ያለውን ደረጃ ይዘው አጠናቀዋል።

የ25 ዓመቷ ኢትዮጵያዊት አትሌት ሀዊ 2:17:25 በማስመዝገብ የውድድሩን ክብረወሰን በ1:45 ማሻሻል ችላለች። ይህም በ2024 አስራ ሁለተኛው የማራቶን ፈጣን ሰዓት ሆኖ ተመዝግቧል። የፍራንክፈርት ማራቶን የቀድሞው ክብረወሰን በኬንያዊቷ አትሌት ቫላሪ ኢያቤ 2019 ላይ የተመዘገበ ነበር።

ሁለተኛ ሆና ያጠናቀቀችው ኬንያዊቷ አትሌት ማዳላይን ማሳይ ያስመዘገበችው 2:18:58 ሰዓትም የግሏ ፈጣን ሰዓትና ከቀድሞው የውድድሩ ክብረወሰን 2:19:10 የተሻለ ፈጣን ሰዓት ሆኖ ተመዝግቧል። ሌላኛዋ ኢትዮጵያዊት አትሌት ሹኮ ገነሞ 2:22:37 በማጠናቀቅ ሦስተኛ ሆና ፈፅማለች።

ከአጭር ርቀት ውድድሮች ጀምሮ አስደናቂ ብቃት ማሳየት የቻለችው ሀዊ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ፊቷን ወደ ማራቶን አዞራለች። በ2023 የዓለም ሀገር አቋራጭ ቻምፒዮና ስድስተኛ ደረጃን ይዛ ያጠናቀቀችው ሀዊ ፍራንክፈርት ላይ በማራቶን ያስመዘገበችው ሰዓት በርቀቱ ትልቅ ስኬቷና ተስፋ እንዲጣልባት ያደረገ ነው።

"የውድድሩን ክብረወሰን ማሻሻል ትልቁ ግቤ ነበር፣ ከ25ኛ ኪሎ ሜትር በኋላ ይህን ግቤን ለማሳካት በቂ አቅም ስለነበረኝ ከተፎካካሪዎቼ ተነጥዬ ወደ ፊት በመውጣት ተጠቅሜበታለሁ፣ በዚህም በጣም ተደስቻለሁ፣ የውድድሩ ጥሩ ድባብም ረድቶኛል፣ በዚህ ውድድር ከ2:16 በታች ማጠናቀቅ እንደሚቻልም ተገንዝቤያለሁ" በማለት ባለድሏ አትሌት ከውድድሩ በኋላ በስፍራው ለነበሩ ሚዲያዎች አስተያየቷን ሰጥታለች።

ከውድድሩ ቀደም ብሎ ከ2:21:17 የፈጠነ ሰዓት ያለው አትሌት አልነበረም። በዚህም ሀዊ በፈለገችው ፍጥነት የመሮጥ እቅድ የነበራት ቢሆንም የውድድሩ አዘጋጆች እስከ 25 ኪሎ ሜትር ድረስ አትሌቶች በጋራ እንዲሮጡ ፍላጎት ነበራቸው። ይህም ታክቲክ ሰርቶ የቦታው ክብረወሰን ሊሻሻል እንደቻለ ተናግራለች።

በፍራንክፈርት ማራቶን ሁለት አትሌቶች ከ2:20 በታች ሲያጠናቅቁ የዘንድሮው የመጀመሪያ ነው። እስከ አስር ባለው ደረጃ ያጠናቀቁ አትሌቶች የግል ፈጣን ሰዓታቸውን ማሻሻላቸውም የዘንድሮውን ውድድር የተለየ አድርጎታል።

በወንዶች መካከል የተካሄደው ውድድር ክብረወሰን ባይመዘገብበትም አዲስ ነገር የታየበት ነበር። ይህም በማራቶን ለመጀመሪያ ጊዜ የተፎካከረው የ22 ዓመቱ ኬንያዊ ቤናርድ ቢዎት በ2:05:54 ማሸነፍ መቻሉ ሲሆን፣ ኢትዮጵያዊው ጎሳ ጫላ 2:07:35 በማጠናቀቅ ሁለተኛ ደረጃን ይዟል። ሌንጮ ተስፋዬ ደግሞ 2:08:02 በመግባት ሦስተኛ ሆኖ የፈፀመ አትሌት ነው።

ገርባ ዲባባ፣ አይቼው ደምሴ፣ ወርቅነህ ሰርባሳ በቅደም ተከተል እስከ ስድስት ያለውን ደረጃ ይዘው ያጠናቀቁ ኢትዮጵያውያን ሆነዋል።

በሁለቱም ፆታ አሸናፊ የሆኑት አትሌቶች ርቀቱን ያጠናቀቁበት ድምር ሰዓት 4:23:19 ሲሆን ይህም በፍራንክፈርት ማራቶን የረጅም ዓመት ታሪክ ፈጣኑ ድምር ሰዓት ሆኖ ተመዝግቧል። በአጠቃላይ በውድድሩ ከ113 ሀገራት የተውጣጡ 13ሺ 939 አትሌቶች የዘንድሮው ፍራንክፈርት ማራቶን ተፎካካሪና ድምቀት እንደነበሩም የውድድሩ አዘጋጆች ገልፀዋል።

"የውድድሩ ክብረወሰን የተሻሻለበትን ፉክክር በማየታችን ተደስተናል፣ ፍራንክፈርት ላይ ፈጣን የማራቶን ሰዓት መመዝገብ እንደሚችልም አረጋግጠናል" በማለት የውድድሩ ዳይሬክተር ፊሊፕ ክሎፕ ለሚዲያዎች አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።